# የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
# የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት
# የሥራ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

ለኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የቀረበ

ጥር 2014

# ማ ው ጫ

ገጽ


| | | |
|---|---|---|
| **I.** | **መ ግ ቢ ያ** | 1 |
| **II.** | **በ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት** | 2 |
| | 2.1 የተረጋጋ የዋጋ ሁኔታ እንዲኖር ማድረግ | 2 |
| | 2.1.1 ባለአንድ አሃዝ የዋጋ ንረት | 2 |
| | 2.1.2 የተረጋጋ የውጭ ምንዛሪ ተመን ማስፈን | 3 |
| | 2.2 ከፍተኛና ቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስገኘት | 6 |
| | 2.3 ጤናማና አስተማማኝ የፋይናንስ ሥርዓት ማስፈን | 7 |
| | 2.4 የተገልጋዮች እርካታና አመኔታ | 15 |
| | 2.5 የባንኩን የፋይናንስ አስተዳደር ማሻሻል | 17 |
| **III.** | **የተከናወኑ ዐበይት ተግባራት፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች** | 19 |
| | 3.1 የተከናወኑ ዐበይት ተግባራት | 19 |
| | 3.2 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች | 20 |
| | **አባሪ ሠንጠረዥ** | **22 - 35** |

# I. መግቢያ

1. በ2013 በጀት ዓመት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ 9 በመቶ ያህል እንደሚያድግ ተተንብዮ የነበረ ቢሆንም፣ በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በአገራችን በተከሰተው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ሳቢያ የኢኮኖሚ ዕድገቱ 6.1 በመቶ ሆኗል፡፡ ይህ ዕድገት እ.ኤ.አ. በ2020 ከተመዘገበው የ4.4 በመቶ የዓለም፣ 3.3 በመቶ የአዳጊ አገሮች እና 3.0 በመቶ ከሰሐራ በታች ካሉ አገራት የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ ጋር ሲነፃፀር በእጅጉ የተሻለ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በ2014 (እ.ኤ.አ. በ2021/22) በጀት ዓመትም የዓለም ኢኮኖሚ በ5.2 በመቶ፣ ከሰሐራ በታች ያሉ አገራት ደግሞ በ3.1 በመቶ እንደሚያንሠራሩ ስለሚጠበቅ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚም በአንፃራዊነት ከአምናው የተሻለ ዕድገት እንደሚያሳይ ተተንብዮአል፡፡

2. በጥቅሉ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በአዋጅ ከተሰጠው ቁልፍ ተግባራትና ኃላፊነት አንፃር የዋጋ ንረትና የውጭ ምንዛሪ ዋጋ ለማረጋጋት፣ የፋይናንስ ዘርፉን ጤናማነት ለመጠበቅና የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነትና አካታችነት የማስፋት፣ የውጭ ምንዛሪ ግኝት ለማጠናከር፣ እንዲሁም ቁጠባና ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት፣ የሥራ ዕድልና የሕዝቡን የነፍስ ወከፍ ገቢ ለማሳደግ እና አስከፊ ድህነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ እርምጃዎችን በመውሰዱ ምክንያት ባለፉት ተከታታይ ዓመታት ለተገኘው ቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

3. በ2014 በጀት ዓመትም ባንኩ ከሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም እና ከ10 ዓመቱ አገራዊ ዕቅድ ጋር የተጣጣመ ዓመታዊ ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ ሥራ ገብቷል፡፡ ከዚህ አንፃር የባንኩ የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት የዕቅድ አፈፃፀም፣ ያጋጠሙ ችግሮችንና የተወሰዱ እርምጃዎችን ያካተተ ሪፖርት በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## II. *በ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት*

### 2.1 የትኩረት መስክ፡- *የተረጋጋ የዋጋ ሁኔታ እንዲኖር ማድረግ*

#### 2.1.1 *የሚጠበቅ ውጤት*፡- *ባለአንድ አሃዝ የዋጋ ንረት*

4. ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ስትራቴጂካዊ ግቦች አንዱ ዋጋን ማረጋጋትና የዋጋ ንረትን በነጠላ አሃዝ መገደብ ነው፡፡ ይህ ስትራቴጂካዊ ግብ የተቀመጠው በዋናነት የብር የመግዛት አቅምን ለመጠበቅ፣ ቁጠባና ኢንቨስትመንት ለማበረታታት፣ የሥራ ዕድል ለማስፋት፣ የገቢ ክፍፍልና የሀብት ድልድል ሚዛናዊ ለማድረግና ሁሉም ተጠቃሚ የሚሆንበትን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ቀጣይነት ለማረጋገጥ ነው፡፡

5. ይህንን ግብ ለማሳካት ባንኩ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ አጋማሽ የዋጋ ንረትን ሁኔታ ለማሻሻል የተለያዩ የገንዘብ ፖሊሲ መሣሪያዎች መጠቀሙን ቢቀጥልም፣ የዋጋ ንረት ለተከታታይ ወራት እየጨመረ መጥቶ ታህሣሥ ወር 2014 መጨረሻ 35.1 በመቶ ደርሷል፡፡ ይህም በሰኔ ወር 2013 መጨረሻ ከተመዘገበዉ 24.5 በመቶ የዋጋ ንረት ጋር ሲነፃፀር የ10.6 በመቶ፣ ባለፈው ዓመት ታህሣሥ ወር ከነበረው 18.2 በመቶ የዋጋ ንረት ጋር ሲነፃፀር ደግሞ የ16.9 በመቶ ከፍተኛ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ ለዓመታዊው የዋጋ ንረት ጭማሪ ምክንያት የሆነው የምግብ ነክ የዋጋ ግሽበት 41.6 በመቶ፣ ምግብ ነክ ያልሆኑ ሸቀጦች ዋጋ 26.6 በመቶ ከፍ በማለቱ ነው፡፡ በተመሳሳይ አማካይ ተንከባላይ ዓመታዊ የዋጋ ንረት አምና ታህሣሥ ወር ከነበረበት 20.3 በመቶ በዘንድሮው ተመሳሳይ ወቅት ወደ 26.8 በመቶ ከፍ ሊል የቻለው ምግብ ነክ የዋጋ ንረት አምና ከነበረበት 23.1 በመቶ ዘንድሮ ወደ 31.8 በመቶ በማሻቀቡ፣ ምግብ ነክ ያልሆነዉ የዋጋ ንረትም ከ17.0 በመቶ ወደ 20.4 በመቶ በመጨመሩ ነዉ፡፡ በተከታታይነት ጭማሪ እያሳየ ለመጣው የዋጋ ግሽበት እንደ ምክንያት ከሚጠቀሱት መካከል፣ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት እጥረት፣ የውጭ ምንዛሪ ተመን በከፍተኛ ሁኔታ እየወረደ መምጣት፣ በበቂ ደረጃ የገንዘብና የፊስካል ፖሊሲ ጥብቅ ያለመሆን፣ ምርትና ምርታማነት በበቂ ሁኔታ አለመጨመር እንዲሁም በአንዳንድ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍሎች የተከሰተው አለመረጋጋት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እነዚህን ተግዳሮቶች ለመቅረፍና የዋጋ ንረቱን ለማርገብ የሚረዱ ጥብቅ የገንዘብ ፖሊሲ እርምጃዎችን ከመውሰዱም ባሻገር ሌሎች የፊስካል ፖሊሲና አስተዳደራዊ እርምጃዎችም በመንግሥት በኩል በቅንጅት እየተወሰዱ ይገኛሉ፡፡

6. ከዚህ ሌላ፣ የገንዘብ ፖሊሲ አካል የሆነው የወለድ ተመን የተረጋጋ፣ የአገሪቱን ተጨባጭ ማክሮ ኢኮኖሚያዊ አመልካቾች ያገናዘበ፣ አስቀማጮችንም ሆነ ተበዳሪዎችን የማይጎዳና የሥራ ዕድልን የሚያሰፋ እንዲሁም የፋይናንስ ተደራሽነትንና አካታችነትን የሚያበረታታና የመንግሥትን የልማት ፖሊሲ የሚደግፍ እንዲሆን ለማድረግ ባንኩ በትኩረት እየሠራ ይገኛል፡፡ በዚህ መሠረት ባንኩ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ

ስድስት ወራት በተቀማጭ ገንዘብ ላይ የሚከፈለው ዝቅተኛ የወለድ መጠን 7.0 በመቶ ሆኖ እንዲቀጥል አድርጓል፡፡ በመሆኑም በተቀማጭ ገንዘብ ላይ የሚከፈለው አማካይ የወለድ ተመን 8.0 በመቶ ደርሷል፡፡ በአንፃሩ፣ ባንኮች የሚያስከፍሉትን የማበደሪያ የወለድ ተመን በራሳቸው እንዲወስኑ በመፈቀዱ የባንኮች ዝቅተኛ የማበደሪያ ተመን 7.0 በመቶ፤ ከፍተኛው 21.50 በመቶ፣ አማካዩ ተመን ደግሞ 14.25 በመቶ ሆኗል፡፡

7. ከዚህ በተጨማሪ፣ መንግሥት ለበጀት ጉድለት ማሟያ ከብሔራዊ ባንክ የሚወስደው ቀጥታ ብድር በዕቅዱ መሠረትና ከዋጋ ንረት ግብ ጋር በተጣጣመ መልኩ መሆኑን ለማረጋገጥ ባንኩ ክትትል አድርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት እስከ በጀት ዓመቱ የመጀመሪያ መንፈቅ መጨረሻ ድረስ መንግሥት ከብሔራዊ ባንክ የወሰደው ቀጥታ ብድር ብር 30 ቢሊዮን ደርሷል፡፡

8. እንደዚሁም የዋጋ መረጋጋትን ለማስፈን ባንኩ የግምጃ ቤት ሠነድ እንደ ከፊል የገንዘብ ፖሊሲ መሣሪያ በመጠቀም ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህ አኳያ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ አጋማሽ በተካሄዱ የግምጃ ቤት ሠነድ ጨረታዎች አማካይነት ብር 312.9 ቢሊዮን ዋጋ ያላቸው ሠነዶችን ለተለያዩ ተቋማት ለመሸጥ ተችሏል፡፡ ይህም የግምጃ ቤት ሠነድ ሽያጭ ከአምና ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ296.1 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ የሠነዶቹ አቅርቦትም በ315.8 በመቶ ጨምሯል፡፡ በዚሁ መሠረት በስድስት ወራት ውስጥ ለመንግሥት በጀት ጉድለት ማሟያ የዋለው የግምጃ ቤት ሠነድ በዋጋ ሲተመን ብር 132.8 ቢሊዮን ሆኗል፡፡

### *2.1.2 የትኩረት መስክ፡- የተረጋጋ የውጭ ምንዛሪ ተመን እንዲኖር ማድረግ የሚጠበቅ ውጤት፡-*

### *ሀ/ የተረጋጋ የውጭ ምንዛሪ ተመን ማስፈን*

9. የተረጋጋ የውጭ ምንዛሪ ተመን መኖር የሀገሪቱን የወጪ ንግድ ተወዳዳሪነት ለማጠናከር፣ የንግድ ሚዛን ለማሻሻል እና የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ለማሳደግ እንደሚረዳ ይታመናል፡፡ ይህንንም ዓላማ ለማሳካት ብሔራዊ ባንክ የሀገሪቱን ተጨባጭ የኢኮኖሚ ዕድገት ደረጃ ያገናዘበ ከፊል አስተዳደራዊና ከፊል ገበያ መር የሆነ የውጭ ምንዛሪ ተመን ፖሊሲ ቀይሶ ተግባራዊነቱን በቅርበት በመከታተል ላይ ይገኛል፡፡

10. በዚህ መሠረት፣ በ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት በኦፊሴላዊ የባንክ ለባንክ የውጭ ምንዛሪ ገበያ አንድ የአሜሪካን ዶላር በአማካይ በብር 46.2567 ተመንዝሯል፡፡ በመሆኑም በተጠቀሱት ወራት ውስጥ የብር ዋጋ ከአሜሪካን ዶላር አኳያ ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በ25.6 በመቶ እንዲወርድ ሆኗል፡፡ እንዲሁም የብር የውጭ ምንዛሪ ዋጋን ለማረጋጋት ባንኩ በየዕለቱ በሚካሄደው የባንክ ለባንክ የውጭ ምንዛሪ ገበያ ቀጥታ ተሳታፊ በመሆን 6.4 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለውጭ ምንዛሪ ግብይት በማቅረቡ የብር ዋጋ ያላግባብ እንዳይዋዥቅ ረድቷል፡፡ ከዚህ ሌላ ባንኩ ከውጭ ለሚገቡ ሸቀጦች በተለይም ለነዳጅና ለመሠረተ ልማት ግንባታና ማስፋፊያ ለሚውሉ ዕቃዎችና መሣሪያዎች ግዥ በድምሩ 2.8 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር አቅርቧል፡፡

## ለ/ በቂ የውጭ ምንዛሪ ክምችት መያዝና ማስተዳደር

11. በቂ የውጭ ምንዛሪ ክምችት መያዝና ማስተዳደር ከብሔራዊ ባንክ ስትራቴጂካዊ ግቦች አንዱ ሲሆን፣ ባንኩ ይህን ግብ ለማሳካት የአገሪቱን የክፍያ ሚዛን እንዲሁም የራሱንና የሌሎች ንግድ ባንኮችን የውጭ ምንዛሪ ፍሰት ትንበያ በማካሄድና አፈፃፀሙንም በመከታተል ወቅታዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶችን አዘጋጅቷል፡፡ በእነዚህም የአፈፃፀም ግምገማዎች መሠረት በ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው መንፈቅ መጨረሻ የአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ መጠባበቂያ ክምችት 1.6 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወይም የ1.3 ወራት የገቢ ሸቀጦችና አገልግሎቶች ወጪ ለመሸፈን የሚበቃ ሆኗል፡፡

12. የውጭ ምንዛሪ መያዝና ማስተዳደርን በተመለከተ ባንኩ አብዛኛው የውጭ ምንዛሪ ሀብት በውጭ አገር ስመጥር ማዕከላዊ ባንኮችና በተለያዩ ታዋቂ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ውስጥ እንዲቀመጥ አድርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ ባንኩ የውጭ ምንዛሪ ግኝትና የውጭ ምንዛሪ መጠባበቂያ ክምችት ለማሳደግ በ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ አጋማሽ ከአገር ውስጥ የወርቅ አምራቾች 211.9 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ዋጋ ያለው የወርቅ ግዢ ፈጽሟል፡፡ ይህም የወርቅ ግዥ ከአምናው ግዢ ጋር ሲነፃፀር በ36.9 በመቶ ያህል ያንሳል፡፡ ምንም እንኳ ባንኩ ወርቅ የሚገዛበትን ዋጋ በማሻሻሉ ማህበራትና ግለሰቦች ከኮንትሮባንድ ይልቅ ለባንኩ መሸጥን እንዲመርጡ በማድረግ ረገድ ባለፈው በጀት ዓመት አመርቂ ውጤት የተገኘ ቢሆንም፤ እነዚህ ማህበራት በእጃቸው ይገኝ የነበረውን የወርቅ ክምችት ለባንኩ ቀደም ሲል በማቅረባቸው ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ከወርቅ የሚገኘው ገቢ እየቀነሰ መጥቷል፡፡

13. ከውጭ ምንዛሪ አያያዝና አስተዳደር ጋር በተያያዘ፣ ባንኩ ውስን የሆነውን የአገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ሀብት አጠቃቀም ለማሻሻል አስመጪ ድርጅቶች የተፈቀደላቸውን የውጭ ምንዛሪ ለተፈቀደለት ዓላማ ስለማዋላቸውና ላኪዎችም የውጭ ምንዛሪን በአግባቡ ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባታቸው ክትትል አድርጓል፡፡ ከዚህ አኳያ ግዴታቸውን በወቅቱ ላልተወጡ አስመጪና ላኪ ድርጅቶች/ግለሰቦች ተጨማሪ የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ እንዳይሰጣቸው የሚያደርግ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ለውጭ ምንዛሪ ቢሮዎችና የውጭ ምንዛሪ በጥሬ ገንዘብ እንዲቀበሉ ለተፈቀደላቸው ሆቴሎችና አስጎብኚ ድርጅቶች ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን፣ ድርጅቶቹ የባንኩን የውጭ ምንዛሪ መመሪያ በአግባቡ ስለመተግበራቸው ክትትል ተደርጓል፣ ስህተቶች ሲከሰቱም የእርምት እርምጃ ተወስዷል፡፡ ከዚህ ሌላ የውጭ ምንዛሪን የሚመለከቱ የተለያዩ መመሪያዎች ወጥነት እንዲኖራቸውና እንዲሻሻሉ ተደርጓል፡፡

14. አገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ከምታገኝባቸው ዋና ዋና ምንጮች መካከል የወጪ ንግድ፣ የውጭ ሐዋላ፣ የውጭ ብድርና ዕርዳታ እንዲሁም ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንት ይገኙበታል፡፡ ከዚህ አኳያ ባንኩ የአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ መጠባበቂያ ክምችት በቂና በአስተማማኝ ደረጃ ላይ እንዲሆን ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት፣ የውጭ ንግድ ክፍለ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴን የሚመለከቱ መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የማጠናቀርና የመተንተን ሥራ በታቀደው መሠረት አከናውኗል፡፡

15. በዚሁ መሠረት በ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ መንፈቅ ከሸቀጦች ወጪ ንግድ 1.9 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፤ ይህም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲወዳደር በ21.3 በመቶ ጨምሯል፡፡ ለዚህ የወጪ ንግድ ገቢ ዕድገት በዋናነት አስተዋጽኦ ካደረጉት የወጪ ምርቶች መካከል ቡና፣ የጥራጥሬ እህሎች፣ አበባ፣ ጫት፣ የሥጋና የሥጋ ውጤቶች፣ የጨርቃ ጨርቅ ውጤቶች፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ይገኙባቸዋል፡፡ በአንፃሩ ከወርቅ፣ ከቅባት እህሎች፣ ከቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ ከቁም እንስሳት፣ ከኤሌክትሮኒክስ፣ ከተፈጥሮ ሙጫ እንዲሁም ከሰም የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢ ቅናሽ አሳይቷል፡፡

16. በተመሳሳይ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ አጋማሽ ከግለሰቦችና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የተሰበሰበው የተጣራ የሐዋላ ገቢ 3.2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ደርሷል፡፡ ይህም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ11.4 በመቶ ጭማሪ ሊያሳይ የቻለው በዋናነት ከመንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የተገኘው ገቢ በ59.4 መቶ በመጨመሩ ሲሆን፣ በአንፃሩ ከግለሰቦች የተገኘው ሐዋላ በ0.4 በመቶ በመቀነሱ ነው፡፡ በተመሳሳይ፣ ከተጣራ መንግሥታዊ የውጭ ሐዋላ የተገኘው 441.8 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት በ57.4 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡

17. በሌላ በኩል፣ የተጣራ የካፒታል ሂሳብ ሚዛን 27.9 በመቶ ጭማሪ አስመዝግቧል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የረጅም ጊዜ የተጣራ ብድር ጉድለት ከ329.7 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወደ 310.4 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ዝቅ በማለቱ እና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት 23 በመቶ ዕድገት በማሳየት 1.6 ቢሊዮን ዶላር በመድረሱ እንዲሁም የአጭር ጊዜ ካፒታል እንቅስቃሴ ከ215.1 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ጉድለት ወደ 258.8 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ትርፍ በማሻቀቡ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ የተጣራ የማዕከላዊ መንግሥት የረጅም ጊዜ ብድር ከ542.7 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ትርፍ ወደ 170.8 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ትርፍ ዝቅ ብሏል፡፡

18. የሸቀጦች ገቢ ንግድን በተመለከተ በግማሽ ዓመቱ 8.5 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወጪ ሆኗል፡፡ ይህም ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከነበረው አሃዝ 24.8 በመቶ ይበልጣል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው ለፍጆታ ዕቃዎች፣ በከፊል ላለቀላቸው ሸቀጦች እና ለነዳጅ የተፈፀመው ክፍያ በቅጭም ተከተል 50 በመቶ፣ 19.6 በመቶ እና 78.6 በመቶ ከፍ በማለቱ ሲሆን፣ በአንፃሩ ለካፒታል ዕቃዎች እና ለጥሬ ዕቃዎች ግዢ የዋለው የውጭ ምንዛሪ የመቀነስ ሁኔታ ይታይበታል፡፡

19. በመሆኑም፣ በሸቀጦች የገቢ እና የወጪ ንግድ መካከል ያለው የንግድ ሚዛን ጉድለት አምና ከነበረበት 5.2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ዘንድሮ ወደ 6.6 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሊሰፋ ችሏል፡፡ በተጠቀሱት ወራት የሸቀጦች የወጪ ንግድ ገቢ ሊሸፍን የቻለው 22.3 በመቶ የሸቀጦች ገቢ ንግድ ወጪን ብቻ ሲሆን፤ ቀሪው ጉድለት የተሸፈነው በሐዋላ፣ በአገልግሎት የወጪ ንግድ ገቢ፣ በውጭ ዕርዳታና ብድር፣ በውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት እንዲሁም በሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ መጠባበቂያ ክምችት ነው፡፡

## *2.2 የትኩረት መስክ፡- ለኢኮኖሚ ዕደገት አመቺ ሁኔታ መፍጠር የሚጠበቅ ውጤት፡- ከፍተኛና ቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስገኘት*

20. ባንኩ ለኢኮኖሚ ዕድገት አመቺ ሁኔታዎችን ከመፍጠር አኳያ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ በባንኩ አነሳሽነት ከዓመታት በፊት የተጀመረውን የኢትዮጵያ መንግሥት የቁጠባ ቦንድ (ታላቁን የሕዳሴ ግድብ ቦንድ) በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ለመሸጥና ለማስፋፋት በተያዘው ዕቅድ መሠረት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ የኢትዮጵያ ልማት

ባንክና አንዳንድ የተመረጡ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የቦንድ ሽያጭ በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚሁ መሠረት እስከ ታህሣሥ ወር 2014 መጨረሻ ድረስ ብር 14.4 ቢሊዮን ዋጋ ያላቸው የህዳሴ ቁጠባ ቦንዶች በሀገር ውስጥ ተሸጠዋል፡፡ ለቦንድ ግዥዎች ተመላሽ የተደረገው ሲቀነስ ቀሪው ገንዘብ ብር 5.6 ቢሊዮን ይሆናል፡፡

21. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የገዛው አዲስ የኮርፖሬት ቦንድ በዋጋ ሲሰላ ብር 23.3 ቢሊዮን፣ ከባቡር ኮርፖሬሽን የገዛው ብር 13.0 ቢሊዮን እና ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የገዛው ብር 2.5 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ በጥቅሉ የኮርፖሬት ቦንድ ሽያጭ በሀገሪቱ እየተካሄዱ ላሉ ትላልቅ የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ትልቅ የፋይናንስ አቅም የፈጠረ የፋይናንስ ምንጭ ሆኗል፡፡ ከዚህ ሌላ፣ በተጠቀሱት ወራት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ዘርፎች ብር 46.9 ቢሊዮን ብድር ለማቅረብ ተችሏል፡፡ ይህም ከዕቅዱ በብር 19 ሚሊዮን ይበልጣል፡፡

## *2.3 የትኩረት መስክ፦ <u>የፋይናንስ ሥርዓቱን መረጋጋት ማስፈን</u>*
## *የሚጠበቅ ውጤት፡ <u>ጤናማና አስተማማኝ የፋይናንስ ሥርዓት</u>*

22. ከብሔራዊ ባንክ ዋና የትኩረት መስኮች አንዱ የፋይናንስ ሥርዓቱ የተረጋጋ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ባንኩ ዓለም አቀፍ ደረጃን በጠበቀ አኳኋን የፋይናንስ ሥርዓቱን ጤናማነት የመከታተል፣ የመቆጣጠርና የመገምገም ሥራዎችን በዕቅዱ መሠረት አከናውኗል፡፡

23. በመሆኑም በ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያዎቹ 6 ወራት ባንኩ ለሁለት አዲስ ባንኮች እና ወደ ባንክ ለተሸጋገሩ ሁለት አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የባንክ ሥራ ፈቃድ በመስጠቱ አጠቃላይ የባንኮች ቁጥር ወደ 24 ከፍ ብሏል፡፡ በተጨማሪም፣ ሌሎች 17 ባንኮች በምስረታ ላይ ሲሆኑ፣ ሌሎች 4 አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ወደ ባንክ ዘርፍ ለመቀላቀል በሽግግር ሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡

24. በ2014 በጀት ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ መጨረሻ 8,038 ቅርንጫፎችና ንዑስ ቅርንጫፎች ያሏቸው 21 ባንኮች በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ልዩ ልዩ የፋይናንስ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል 19 የግል ሲሆኑ፣ 2 ደግሞ የመንግሥት ባንኮች ናቸው፡፡ እነዚህ ባንኮች ቅርንጫፎቻቸውን በመላ ሀገሪቱ ለማስፋፋት ርብርብ በማድረጋቸው የጠቅላላ ቅርንጫፎችና ንዑስ ቅርንጫፎች ብዛት 16.54 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት አሳይቷል፡፡ በመሆኑም፣

በአሁኑ ወቅት አንድ የባንክ ቅርንጫፍ ለ14,307 ተጠቃሚዎች አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ የባንክ ቅርንጫፎች ውስጥ 2,092 (26 በመቶ) የሚሆኑት የሁለቱ የመንግሥት ባንኮች ቅርንጫፎች ሲሆኑ ፣ ቀሪዎቹ 5,946 (74 በመቶ) የግል ባንኮች ድርሻ ናቸው፡፡

25. ከባንክ ቅርንጫፎችና ንዑስ ቅርንጫፎች መስፋፋትና ከቁጠባ ባህል መሻሻል ጋር ተያይዞ የባንክ ደንበኞች ቁጥርም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ይገኛል፡፡ ከዚህ አኳያ፣ አምና 55.73 ሚሊዮን የነበረው የአስቀማጮች ሂሳብ ቁጥር ዘንድሮ በተመሳሳይ ወቅት የ29.84 በመቶ ዕድገት በማሳየት 72.36 ሚሊዮን ደርሷል፡፡ በተመሳሳይ፣ የተበዳሪዎች ቁጥር ከ272,115 ወደ 347,350 ማደጉ የ27.7 በመቶ ዓመታዊ ጭማሪ መኖሩን ያመለክታል፡፡

26. ከዚህ ሌላ፣ ባንኮች የሚሰበስቡት አጠቃላይ የተቀማጭ ገንዘብ ክምችት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል፡፡ በዚህም መሠረት በ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ አጋማሽ መጨረሻ በሁሉም ባንኮች የተሰበሰበው የተቀማጭ ገንዘብ ብር 1.5 ትሪሊዮን ደርሷል፤ ዓመታዊ ጭማሪውም 22.1 በመቶ ሆኗል፡፡ ከአጠቃላይ የተቀማጭ ገንዘብ ክምችት ውስጥ ብር120.1 ቢሊዮን የተሰበሰበው በዘንድሮው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ውስጥ ነው፡፡ ይህም ከአምና ተመሳሳይ ወቅት አሃዝ የብር 63.5 ቢሊዮን ብልጫ አለው፡፡ ከአጠቃላይ ተቀማጭ ገንዘብ ክምችት ውስጥ ብር 651.3 ቢሊዮን (44.1 በመቶ) ያህሉ በግል ባንኮች፤ ቀሪው ብር 825.7 ቢሊዮን (55.9 በመቶ) በመንግሥት ባንኮች የተሰበሰበ ነው፡፡ ከዚህ ተቀማጭ ገንዘብ ውስጥ 32.4 በመቶ በተንቀሳቃሽ፣ 60.3 በመቶ በቁጠባና 7.3 በመቶ በጊዜ ገደብ ተቀማጭ ሂሳቦች ውስጥ ይገኛል፡፡

27. ከዚህ በተጨማሪ፣ በግማሽ ዓመቱ መጨረሻ፤ ሁሉም ንግድ ባንኮች ብር 146.8 ቢሊዮን አዲስ ብድር (የቦንድ ግዥን ጨምሮ) ሰጥተዋል፡፡ ይህ የብድር መጠን ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ብድር በ5.5 በመቶ ያንሳል፡፡ እንደዚሁም፣ የሁሉም ባንኮች ጠቅላላ የብድር ክምችት (ቦንድን ጨምሮ) ብር 1.4 ትሪሊዮን የደረሰ ሲሆን፣ ይህም ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር በ16.8 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡ ከዚህ የብድር ክምችት ውስጥ 53.5 በመቶ ያህሉ በግል ድርጅቶች፤ 46.5 በመቶ ደግሞ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች እጅ የሚገኝ ነው፡፡ በተመሳሳይ በተጠቀሱት 6 ወራት ሁሉም ባንኮች (ተመላሽ ቦንዶችን ጨምሮ) ብር 125.7 ቢሊዮን ተመላሽ ብድር ሰብስበዋል፡፡ ይህም የብድር ተመላሽ ከአምናው በ68.4 በመቶ ከፍ ያለ መሆኑ፣ የኮቪድ ወረርሽኝ ቢኖርም፣ የባንኮች ብድር የማስመለስ አቅም ተጠናክሮ መቀጠሉን ያመለክታል፡፡

28. አጠቃላይ የፋይናንስ አመልካቾችን በተመለከተ፣ የባንኮች (ልማት ባንክን ሳይጨምር) ጠቅላላ ካፒታል ብር 137.89 ቢሊዮን የደረሰ ቢሆን፣ ይህም ከአምናው አሃዝ በ22 በመቶ ያህል ማደጉን ያሳይል፡፡ እንዲሁም የባንኮቹ አጠቃላይ ትርፍ (ከታክስ በፊት) ብር 24.79 ቢሊዮን በመድረሱ ካለፈው ዓመት 60.6 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ የልማት ባንክን ሳይጨምር የባንኮቹ የማይመለሱና አጠራጣሪ ብድሮች ከአጠቃላይ ብድር አኳያ ሲገመገም፣ 6.02 በመቶ ሆኗል፡፡ ይህም ብሔራዊ ባንክ ካስቀመጠው 5 በመቶ ጣሪያ በላይ መሆኑ እስከዚህም አሳሳቢ ባይሆንም ሊታረም ግን የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ በተጨማሪም፣ የባንኮች የገንዘብ አከል ንብረት ጥምርታ (Liquidity Ratio) ቢያንስ 15 በመቶ እንዲሆን ታቅዶ ከዕቅድ በላይ 28.67 በመቶ፤ የካፒታል ብቃት ጥምርታ ደግሞ ብሔራዊ ባንክ ካስቀመጠው 8 በመቶ ወለል በላይ 16.52 በመቶ መሆኑ ሊበረታታ የሚገባ ውጤት ነው፡፡ ከእነዚህም የፋይናንስ አመልካቾች በመነሣት የባንክ ዘርፍ ትርፋማ፣ ጤናማና የተረጋጋ ነው ማለት ይቻላል፡፡

29. ከዚህ ሌላ፣ የክሬዲት ሪፈረንስ ቢሮ መቋቋምና ሥራ ላይ መዋል ባንኮች ስለ ደንበኞቻቸው የብድር ታሪክ እና ተጋላጭነት የተሻለ መረጃ እንዲኖራቸውና በዕውቀት ላይ የተመሠረተ የብድር ትንተና እንዲሠሩ በማገዝ የፋይናንስ ዘርፍ ጤናማነት እንዲጠበቅ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

30. **<u>የኢትዮጵያ ልማት ባንክን በተመለከተ</u>**፡- ባንኩ በመላ አገሪቱ ባሉት 82 ቅርንጫፎችና ንዑስ ቅርንጫፎች አማካይነት ለተለያዩ ብድር ጠያቂዎች የብድር አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በ2014 በጀት ዓመት ታህሣሥ ወር መጨረሻ የባንኩ የብድር ክምችት ብር 54.4 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ ይህም ከአምና ተመሳሳይ ወቅት በ2.0 በመቶ ይበልጣል፡፡ በተመሳሳይ ባንኩ በስድስት ወራት የሰጠው ብር 2.4 ቢሊዮን ብድር ከአምናው በ42.1 በመቶ ሲያንስ፣ የሰበሰበው ብር 4.1 ቢሊዮን ብድር ግን በ25.7 በመቶ ጨምሯል፡፡

31. ከዚህ ሌላ፣ የባንኩ ጠቅላላ ሀብት ብር 119.52 ቢሊዮን፣ ካፒታል ደግሞ ብር 29.16 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ የማይመለስና አጠራጣሪ ብድር ከአጠቃላይ ብድር አኳያ ሲታይ 28.50 በመቶ ሲሆን፣ ይህም ብሔራዊ ባንክ ካስቀመጠው 15 በመቶ ከፍ ያለ መሆኑ፣ ባንኩ የፋይናንስ አቋሙንና አሠራሩን ለማሻሻል ገና ብዙ ጥረት ማድረግ እንዳለበት አመላካች ነው፡፡

## ሰ/ የኢንሹራንስ ዘርፍ እንቅስቃሴ

32. በ2014 በጀት ዓመት ታህሣሥ ወር መጨረሻ የመድን ኩባንያዎች ቁጥር 18 የነበረ ሲሆን፣ ከእነዚህ መካከል ከአንዱ በቀር 17ቱ የግል ናቸው፡፡ የእነዚህ የመድን ኩባንያዎች ቅርንጫፎች ብዛት በታህሣሥ 2014 መጨረሻ 667 ደርሷል፡፡ ከ18ቱ የኢንሹራንስ ድርጅቶች በተጨማሪ፣ 2,412 የመድን ሽያጭ ወኪሎች፣ 62 የመድን ደላሎች፣ 105 ጉዳት ገማቾች እና 3 የመድን መርማሪዎች በኢንሹራንስ የንግድ ዘርፍ ተሠማርተው አገልግሎት እየሰጡ ናቸው፡፡ እንደዚሁም፣ 1 የጠለፋ ዋስትና (Reinsurance) ኩባንያ ተቋቁሞ ሥራ ላይ ይገኛል፡፡

33. በ2014 መስከረም ወር መጨረሻ የመድን ኩባንያዎቹ ጠቅላላ ሀብት ብር 42.50 ቢሊዮን፣ ካፒታል ብር 11.66 ቢሊዮን፣ ኢንቨስትመንት ብር 18.90 ቢሊዮን፣ ጠቅላላ የዐረቦን ገቢ ብር 4.22 ቢሊዮን፣ ትርፍ ደግሞ ብር 503 ሚሊዮን ደርሷል፡፡ ይህም ጠቅላላ ሀብት 38.94 በመቶ፣ ካፒታል 13.45 በመቶ፣ ኢንቨስትመንት 21.82 በመቶ፣ ጠቅላላ ዐረቦን 29.31 በመቶ እና ትርፍ ደግሞ 26.17 በመቶ ዕድገት ማሳየታቸውን ያመለክታል፡፡ ከዚህ ሌላ፣ የመድን ኢንዱስትሪው ዕዳን የመክፈል አቅም (Solvency Margin) 304 በመቶ የደረሰ ሲሆን፣ ይህም ብሔራዊ ባንክ ካስቀመጠው 100 በመቶ ወለል በላይ ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ ከተጠቀሱት የፋይናንስ አመልካቾች ግምገማ በመነሣት የኢንሹራንስ ዘርፍ የተረጋጋና ጤናማ ነው ማለት ይቻላል፡፡

## ሐ/ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት እንቅስቃሴ

34. እስከ መስከረም 2014 መጨረሻ የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ቁጥር 43 የደረሰ ሲሆን፣ የቅርንጫፎቻቸውና የንዑስ ቅርንጫፎች ብዛት ደግሞ 2,195 ሆኗል፡፡ እነዚህ የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ለደንበኞቻቸው የቁጠባ፣ የብድር እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ ናቸው፡፡ ከእነዚህ የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት መካከል ዘጠኙ የሞባይል እና ኤጀንት ባንኪንግ አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን፣ በጥቅሉ በ22,464 ወኪሎቻቸው (ኤጀንቶች) አማካይነት ከ2.9 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ አካውንቶችን ከፍተው ለደንበኞቻቸው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

35. እነዚህ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት እስከ መስከረም 2014 ያሰባሰቡት ቁጠባ ብር 52.30 ቢሊዮን፣ በደንበኞች እጅ ያለ ጠቅላላ ብድር ብር 70.69 ቢሊዮን፣ ጠቅላላ ሀብት ብር 105.15 ቢሊዮን እና ካፒታል ብር 29.5 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ ይህም ካለፈው በጀት ዓመት

ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የቁጠባ መጠን 11.5 በመቶ፣ በደንበኞች እጅ ያለ ጠቅላላ ብድር 9.4 በመቶ፣ ካፒታል 49.7 በመቶ እንዲሁም ጠቅላላ ሀብት 12.6 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡ የብድር ደንበኞች ቁጥር ግን በኮቪድ-19 እና በአንዳንድ አካባቢዎች በተከሰተው ግጭት እንዲሁም በአንዳንድ ተቋማት በተደረገ የቁጥር ማስተካከያ ምክንያት ባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከነበረበት ደረጃ በ11.7 በመቶ ዝቅ ብሎ 4.75 ሚሊዮን ሆኗል፡፡ በሌላ በኩል በእነዚህ ተቋማት የሚንቀሳቀሰው የቁጠባ ሂሳብ ብዛት የ6.9 በመቶ ዕድገት በማሳየት 23.34 ሚሊዮን ደርሷል፡፡

36. ከዚህ ሌላ፣ እነዚህ የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት በመስከረም 2014 መጨረሻ ያሰባሰቡት ጠቅላላ ገቢ ብር 3.3 ቢሊዮን ሲሆን፣ ብር 0.51 ቢሊዮን የተጣራ ትርፍ አስመዝግበዋል፡፡ እንዲሁም የተቋማቱ የካፒታል ብቃት ጥምርታ ቢያንስ 12 በመቶ እንዲሆን ታቅዶ ከዕቅዱ በላይ 35.6 በመቶ፣ የገንዘብ አከል ንብረት ጥምርታ (Liquidity Ratio) ቢያንስ 20 በመቶ እንዲሆን ታቅዶ ከእቅዱ በላይ 42.7 በመቶ ሆኗል፡፡ በሌላ በኩል በዘርፉ ያለው የተበላሸ ብድር ጥምርታ ቢበዛ 5 በመቶ እንዲሆን ታቅዶ ከዕቅዱ በላይ 8.2 በመቶ ደርሷል፡፡ ከእነዚህ ዋና ዋና የፋይናንስ ጤናማነት አመልካቾች አንፃር ሲታይ፣ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ዘርፍ አሁንም የተረጋጋ እና ጤናማ ቢሆንም፣ በብድር አመላለስ ረገድ ግን የኮቪድ-19 ወረርሽኝ እና በአንዳንድ አካባቢዎች (የትግራይ ክልልን ጨምሮ) የሚታየው ግጭት አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

37. ከዚህ በተጨማሪ፣ ስድስቱ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኩባንያዎች እስከ መስከረም 2014 መጨረሻ ለ4,795 ተገልጋዮች የብር 1.56 ቢሊዮን የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡ የኩባንያዎቹ ጠቅላላ ሀብት ብር 4.66 ቢሊዮን፣ ካፒታላቸው ደግሞ ብር 2.33 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ ይህም ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር ጠቅላላ ሀብት 13.4 በመቶ ማደጉን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል የኩባንያዎቹ የካፒታል ብቃት ጥምርታ ቢያንስ 10 በመቶ እንዲሆን ታቅዶ ከዕቅዱ በላይ 59.4 በመቶ፣ የተበላሸ የሊዝ ፋይናንስ ጥምርታ ደግሞ ቢበዛ 5 በመቶ መሆን ሲገባው አፈፃፀሙ 5.8 በመቶ ሆኗል፡፡ ስለሆነም የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ ገና ጀማሪ ቢሆንም ጤናማ እና የተረጋጋ ነው ማለት ይቻላል፡፡

### መ/ <u>የክፍያ ሥርዓትን በተመለከተ</u>

38. ባንኩ በኢትዮጵያ ዘመናዊ የክፍያ ሥርዓት እንዲዘረጋና አስተማማኝና ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ ያስቀመጠውን ስትራቴጂካዊ ግብ ለማሳካት የተቀናጁ የክትትልና የቁጥጥር ሥራዎችን በዕቅዱ መሠረት አከናውኗል፡፡ ከዚህ አኳያ በክፍያ ተጠቃሚ አካላት ዘንድ የሚከናወኑ የሒሣብ እንቅስቃሴዎችን ቅልጥፍና ለማሣለጥ የሚያስችሉ መጠነ ሰፊ የክፍያ መሠረተ ልማት ዝርጋታዎች በፋይናንስ ተቋማት አማካኝነት ተካሂደዋል፡፡ ከዚህ ሌላ፣ የክፍያ አገልግሎቱን ይበልጥ ተደራሽና ቀልጣፋ ለማድረግ፤ የቴሌኮም መሠረተ ልማት በሚደርስባቸው ሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች የሚገኙ አዲስም ሆኑ ነባር የባንክ ቅርንጫፎች፣ በኮር ባንኪንግ ቴክኖሎጂ አማካኝነት ከዋና መ/ቤቶቻቸው ጋር እንዲተሳሰሩ ተደርጓል፡፡ የሁሉም ባንኮች ዋና መ/ቤቶች፣ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ እና የማዕከላዊ የካርድ ስዊች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከሚያስተዳድረው የክፍያ ሥርዓት ጋር በመተሳሰራቸው ለሁሉም ተሳታፊ አካላት ወጥና ቀልጣፋ የእርስ በርስ የክፍያ፣ ሂሳብ የማጣራትና የማወራረድ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ የዚህ በብሔራዊ ባንክ የሚተዳደረው ዘመናዊ የክፍያ ሥርዓት (EATS) ደህንነት እና አስተማማኝነት ለፋይናንስ ሥርዓቱ ጤንነት እጅግ አስፈላጊ በመሆኑና ባንኩ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከፍተኛ ክትትል እና ቁጥጥር በማድረጉ በክፍያ ሥርዓቱ ላይ ምንም ዓይነት የጎላ ችግር አላጋጠመም፡፡

39. የዲጅታል የክፍያ መፈፀሚያ መሣሪያዎችን ተደራሽነት ለማስፋትና በሁሉም የፋይናንስ ተቋማት ዘንድ ያለውን የክፍያ መሠረተ ልማት በጋራና በትብብር ለመጠቀም በሚያስችለው ብሔራዊ ማዕከላዊ ስዊች ኩባንያ አማካይነት በተዘረጋው ሥርዓት የተነሣ ቀደም ሲል በኤቲኤም ማሽን ብቻ ተወስኖ የነበረዉ የክፍያ ተናባቢነት በበጀት ዓመቱ ውስጥ ወደ የክፍያ ነቁጥ (POS) ማሽን ለማስፋት ተችሏል፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ በአንድ ባንክ የክፍያ ካርድ በሌላኛዉ ባንክ የግብይት/የክፍያ ነቁጥ ማሽን ክፍያ መፈፀም የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ሆኖም ግን ይህ አገልግሎት የበለጠ አስተማማኝ እና ውጤታማ እንዲሆን ከንግድ ባንኮች እና ከብሔራዊ ስዊች በኩል ከፍተኛ ጥረት ይጠይቃል፡፡ በተጨማሪም የክፍያ ተናባቢነትን ወደ ሞባይል እና ሌሎች የክፍያ አማራጮች ለማስፋት የሚያስችል □ሮጀክት ተቀርጾ በተሳታፊ ባንኮችና በማዕከላዊ ስዊች አማካይነት ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

40. ባንኩ ባለፈዉ የበጀት ዓመት የክፍያ መፈፀሚያ ኣዉጪዎችንና የክፍያ ኦ□ሬተሮችን የሚመለከቱ ሁለት መመሪያዎች ያወጣ ሲሆን፤ በነዚህ መመሪያዎች ላይም በበጀት ዓመቱ ውስጥ አስፈላጊዉ ገለጻ ለሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት በተደጋጋሚ ተሰጥቷል፡፡ እነዚህም መመሪያዎች የክፍያ ሥርዓቱን ዕድገት ትርጉም ባለዉ ደረጃ እንደሚለውጡ ይጠበቃል፡፡

41. የሁለቱን መመሪያዎች መውጣት ተከትሎ 11 የፍቃድ ጥያቄዎች በበጀት ዓመቱ ውስጥ የቀረቡ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት ለአንድ የክፍያ ሠነድ አውጪ እና ለሁለት የክፍያ ኦ□ሬተሮች ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ለስምንት የክፍያ ኦፕሬተሮች ፍቃድ ለመስጠት ቅድመ ሁኔታዎች ተጠናቀዋል፡፡ ኢትዮ ቴሌኮም ለመጀመሪያ ጊዜ በሞባይል ገንዘብ አገልግሎት ሰጪነት ዘርፍ እንዲሠማራ የሥራ ፈቃድ ተሰጥቶታል፡፡

42. የዲጅታል ክፍያን ከማስፋፋት ባሻገር የፋይናንስ ተደራሽነትንና አካታችነትን ለማጠናከር በተወሰዱ እርምጃዎች የተነሣ የባንክና የዲጂታል ክፍያ አገልግሎቶች በመስፋፋት ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚሁ መሠረት እስከ ታህሣሥ ወር 2014 መጨረሻ ድረስ ንግድ ባንኮች የተከሏቸው የክፍያ መፈጸሚያ ማሽኖች (ኤቲ ኤም) ቁጥር 6,642፣ አጠቃላይ የግብይት ነቁጦች (ፒኦኤስ) ብዛት 10,951 ደርሷል፡፡ እንዲሁም ከ27.1 ሚሊዮን የሚበልጡ የክፍያ ካርዶች በባንኮች በኩል የተሰጡ ሲሆን፣ ይህም አሃዝ ከአምናው 24.4 በመቶ ይበልጣል፡፡ ከዚህ ሌላ፣ 70,591 ወኪሎች በፋይናንስ ተቋማት እና በኢትዮ ቴሌኮም ተመልምለው የሞባይል ገንዘብ አገልግሎት መስጠት በመጀመራቸው የሞባይል ገንዘብ አገልግሎት ለተጠቃሚዎች በቀላሉ እንዲዳረስ ለማድረግ እና የፋይናንስ አካታችነትን ለማረጋገጥ የተጀመረውን ጥረት በማሳካት ረገድ ጉልህ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ የሞባይል ባንኪንግ ተጠቃሚዎች ቁጥር 14.6 ሚሊዮን የደረሰ ሲሆን፣ ከ3.5 ሚሊዮን በላይ የባንክ ደንበኞች የኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ቁጥራቸውም በእጥፍ አድጓል፡፡ ከ7,525 የሚበልጡ የባንክ ቅርንጫፎች በኮር ባንኪንግ ወይም በኤሌክትሮኒክ ክፍያ መረብ የተሳሰሩ በመሆናቸው፣ ከአንዱ ባንክ ወደ ሌላው ወይም በአገሪቱ አንድ ጥግ ከሚገኝ የባንክ ቅርንጫፍ በሌላ ጥግ ወዳሉ የቅርንጫፍ ደንበኞች ገንዘብ ማስተላለፍ የሚቻልበት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

43. ባንኩ በተያዘዉ የበጀት ዓመት የመጀመሪያ መንፈቅ የክፍያ ሥርዓትን በተመለከተ ካከናወናቸዉ ሥራዎች ውስጥ ብሔራዊ የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት ስትራቴጂ መቅረጽ ይገኝበታል፡፡ በመሆኑም ባሁኑ ጊዜ የብሔራዊ ዲጂታል ክፍያ ሥርዓት ስትራቴጂ ተጠናቆ የፀደቀ ሲሆን፣ የትግበራ ሂደቱ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን እየተከናወነና የክትትልና ግምገማ ሪፖርት እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡

44. የባንክ ለባንክ ክሬዲት ትራንስፈር አገልግሎት ለመስጠት በተያዘዉ ዕቅድ መሠረት አብዛኞቹ ቅድመ ሁኔታዎች የተጠናቀቁ ሲሆን፣ የቴክኒክና ኦ□ሬሽን ቅድመ ሁኔታዎችን ያሟሉ የተወሰኑ ባንኮች አገልግሎቱን እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

## ሠ/ የፋይናንስ ተደራሽነትና አካታችነት በተመለከተ

45. የፋይናንስ ተደራሽነትና አካታችነትን ለማጠናከር በተወሰዱ እርምጃዎች የባንክና የክፍያ አገልግሎቶች በመስፋፋት ላይ ሲሆኑ፣ በዚያ መጠን የፋይናንስ ተደራሽነትና አካታችነትም እየተሻሻለ ይገኛል፡፡

46. የፋይናንስ ተቋማት የሂሳብ ቁጥር (ሞባይል ገንዘብን ጨምሮ) አምና መስከረም 2013 ወር ላይ ከነበረበት 89 ሚሊዮን ዘንድሮ በተመሳሳይ ወቅት ወደ 124 ሚሊዮን በማደግ የ40 በመቶ ዓመታዊ ጭማሪ አስመዝግቧል፡፡ ይህም በብር ለውጥ ምክንያት የተፈጠረውን 7.2 ሚሊዮን አዲስ የሂሳብ ቁጥር ያካትታል፡፡ ከዚህ ሌላ፣ ለ100 ጎልማሶች ይደርስ የነበረው የሂሳብ ቁጥር ከ162 ወደ 218 ከፍ ማለቱ የፋይናንስ ተደራሽነትና ተጠቃሚነት እያደገና እየተስፋፋ መምጣቱን ያመላክታል፡፡

47. በተጨማሪም፣ የፋይናንስ አገልግሎት መዳረሻዎች (ቅርንጫፎች፣ ወኪሎች፣ ATM እና POS) ቁጥር መስከረም 2013 ከነበረበት 71,500 በ45% አድጎ መስከረም 2014 መጨረሻ ወደ 103,532 ደርሷል። በመሆኑም፣ የፋይናንስ አገልግሎት መዳረሻዎቸ ቁጥር ለ100,000 ሰዎች ከ130 ወደ 182 ከፍ ብሏል ።

48. በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የተመሠረተ የዋስትና መብት አዋጅ መውጣትን ተከትሎ የመያዣ መዝገቡን ሥርዓት ለመመሥረት በዕቅድ የተያዙ ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚሁ መሠረት፤ እስካሁን ከ42,000 በላይ የሚሆኑ በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የተመሠረቱ አዳዲስ የብድር አገልግሎቶች ተመዝግበዋል፡፡

49. ሁለተኛው ዙር ብሔራዊ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ በብሔራዊ የፋይናንስ አካታችነት ምክር ቤት የፀደቀ ሲሆን፣ የስትራቴጂው ሠነድ በቅርቡ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ቀርቦ እንደሚፀድቅ ይጠበቃል፡፡

50. ከ2015 – 2025 የሚዘልቅ ብሔራዊ የፋይናንስ ትምህርት ስትራቴጂ በይፋ ሥራ ለማስጀመር፤ ቅድመ ዝግጅቱ ተጠናቋል፡፡ የዚህ ስትራቴጂ ዓላማ አሁን ያለውን 47 በመቶ የፋይናንስ ዕውቀት ወደ 75 በመቶ ከፍ በማድረግ አጠቃላይ የፋይናንስ አካታችነትን ማሳደግ ነው።

## ረ/ *የከረንሲ አስተዳደርን በተመለከተ*

51. ባንኩ በከረንሲ አስተዳደር ረገድ ከሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት መካከል ገንዘብ ማሳተም፣ ገንዘብ ማሠራጨት፣ አሮጌ ገንዘብ መሰብሰብና አሮጌ የገንዘብ ኖቶችን ማስወገድ ሲሆን፣ በተጨማሪም ከወርቅ እና ከውጭ ምንዛሪ ግዥ/ሽያጭ ጋር የተያያዙ ሥራዎችን በተያዘላቸው ዕቅድ መሠረት አከናውኗል፡፡

52. ከዚህ አኳያ፣ ባንኩ እስከ በጀት ዓመቱ የመጀመሪያ አጋማሽ ድረስ የኢኮኖሚውን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ብር 59.13 ቢሊዮን መጠን ያለው ገንዘብ በክልሎችና በአዲስ አበባ በሚገኙ የባንክ ቅርንጫፎች አማካኝነት አሠራጭቷል፡፡ ከዚህ ሌላ፣ በባንኩ ተከማችቶ ከሚገኘው ከፍተኛ መጠን ያለው ነባሩ ገንዘብ ውስጥ በግማሽ ዓመቱ መጨረሻ ብር 103.68 ቢሊዮን ዋጋ ያላቸው የገንዘብ ኖቶች የተመረጡ ሲሆኑ፣ ከዚህ ውስጥ ብር 48.35 ቢሊዮን ዋጋ ያላቸው ተወግደዋል፡፡ በተጨማሪም 211.9 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ዋጋ የሚያወጣ የተለያየ የጥራት ደረጃ ያለው ወርቅ ተገዝቶ ወደ ውጭ ሀገር ተጓጉዟል፡፡

## 2.4 *የትኩረት መስክ*:- *የአሠራር ልህቀት ማሳየት*

### *የሚጠበቅ ውጤት*:- *የተገልጋዮች እርካታና አመኔታ*

#### 1/ *የለውጥ ማኔጅመንትን ማጎልበትና የመልካም አስተዳደር ሥርዓት አተገባበር*

53. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከለውጥ ሥራ ማኔጅመንትና የባለድርሻ አካላትን እርካታ ከማሳደግ አኳያ በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፤ ከእነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው:-

- ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣውን የደንበኞች ፍላጎት ለማርካት እና አስተማማኝ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል ባንኩ ሲጠቀምበት የነበረውን የዜጎች ቻርተር ሠነድ የመከለስ ሥራ አጠናቆ ሠነዱ ለባንኩ የውስጥና የውጭ ደንበኞች ተሠራጭቷል፡፡
- ከባንኩ ባለድርሻ አካላትጋር የሚደረግ የውይይት የጊዜ ሠሌዳ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡
- ለውጭና ለውስጥ ባለድርሻ አካላት የተለያዩ የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ተሰጥተዋል፡፡ እንዲሁም ከ2,500 ለሚበልጡ ተጠቃሚዎች እና ከ155 በላይ ለሚሆኑ አጥኚዎች/ተመራማሪዎች አስፈላጊው መረጃ ተሰጥቷል፡፡

- በባንኩ ውስጥ የ360 ድግሪ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ትግበራን ከማስተባበርና ከመደገፍ ባሻገር የ2013 በጀት ዓመት የውስጥና የውጭ የባለድርሻ አካላት እርካታ የዳሰሳ ጥናት የተዘጋጀ ሲሆን፣ የ2014 በጀት ዓመት የዳሰሳ ጥናት ተገባዷል፡፡

- የአገሪቱን የአሥር ዓመት ብሔራዊ የልማት ዕቅድ ሠነድ መነሻ በማድረግ ባንኩ የራሱን ቀጣይ የአሥር ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ አዘጋጅቶ፣ በሠነዱ ላይ በየደረጃው ውይይት ከተካሄደ እና ከዳበረ በኋላ በባንኩ ቦርድ እንዲፀድቅ ተደርጓል፡፡ በፀደቀው የአስር ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ላይ የተቀመጡ ግቦችንና ዒላማዎችን መሠረት በማድረግም የተዘጋጀው የባንኩ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ በትግበራ ላይ ይገኛል፡፡

- የ100 ቀን ዕቅድና አፈፃፀም ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ተልኳል፡፡

- በባንኩ ውስጥ የሚገኙ ሴት ሠራተኞች ከወሊድ ጋር በተገናኘ የሚደርስባቸውን እንግልት ለመቀነስ የሕፃናት ማቆያ ለመገንባት ዝግጅቱ ተጠናቋል፡፡ እንዲሁም ለባንኩ ሴት ሠራተኞች የምክር አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡

- በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ከተፈጠረው ያለመረጋጋት ጋር በተያያዘ ለጀግናው የመከላከያ ሠራዊታችን እያንዳንዱ የባንክ ሠራተኛ የአንድ ወር ደመወዙን እንዲያዋጣ ተደርጎ ከብር 15 ሚሊዮን በላይ በእርዳታ መልክ ተለግሷል፡፡ በጦርነቱ ምክንያት ከቀዬአቸው ለተፈናቀሉ ዜጎች ከባንኩ የማኔጅመንት አባላትና ሠራተኞች በመጀመሪያው ዙር በርካታ አልባሳትን እንዲሁም ከ165 ሺህ ብር በላይ ገንዘብ በማሰባሰብ እና የተለያዩ የምግብ እህሎችን በመግዛት በቀይ መስቀል በኩል እንዲላክ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ባንኩ በሁለተኛው ዙር የእርዳታ ማሰባሰብ ሥራ በጥሬ ገንዘብ ከ2 ሚሊዮን 961 ሺህ ብር በላይ፣ እንዲሁም የተለያዩ አልባሳትን፣ ምግቦችንና የመገልገያ ቁሳቁሶችን በማሰባሰብ በአማራና በአፋር ክልል ለሚገኙ ተፈናቃዮች ግንባር ድረስ በመሄድ ድጋፍ አድርጓል፡፡ ከዚህ ሌላ ሦስት ጊዜ ለመከላከያ ሠራዊት የደም ልገሣ ተደርጓል፡፡

### *ለ/ <u>የሰው ኃይል ልማትና የግብአት አቅርቦት</u>*

54. በ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ 6 ወራት በአጠቃላይ 156 ክፍት የሥራ መደቦች በቅጥር (18)፣ በደረጃ ዕድገት (86)፣ በዝውውር (21) እና በተጠባባቂነት (31) ተሞልተዋል፡፡

በተመሳሳይ በግማሽ ዓመቱ ውስጥ 3 ሠራተኞች በጡረታ፣ 2 በራስ ጥያቄ፣ በድምሩ 5 ሠራተኞች ከባንኩ ጋር ያላቸውን ውል አቋርጠዋል፡፡

55. በግማሽ ዓመቱ ውስጥ በውጭ አገር ሊደረጉ የታቀዱ የልምድ ልውውጦች፣ ሴሚናሮች እና ልዩ ልዩ ሥልጠናዎች በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ባይሳኩም፣ በበይነ መረብ አማካይነት 23 ሠራተኞች በተለያዩ ኮርሶች እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ የአገር ውስጥ ሥልጠናን በተመለከተ በኢትዮጵያ የፋይናንስ ጥናት ተቋም በኩል 59 ሠራተኞች እንዲሰለጥኑ ሆኗል፡፡

56. በግብአት አቅርቦት ረገድ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት ለአብዛኞቹ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የግዢ ጨረታ ወጥቶ በግምገማ ላይ ሲሆን፣ የተወሰኑ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዢም ተፈጽሟል፡፡

57. የባንኩን የኢንፎርሜሽን ሥርዓት አስተዳደር ዘመናዊና ቀልጣፋ ለማድረግ በባንኩ ውስጥ የተዘረጋውን የመሠረተ ልማት ደህንነት ከመጠበቅ ባሻገር የኢንፎርሜሽን ሥርዓት ተደራሽነትን የማስፋፋትና ዘመናዊ የማድረግ እንዲሁም የኢንፎርሜሽንና የቴክኖሎጂ አስተዳደርን፣ የሥጋት አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓትን የማጠናከርና የተጠቃሚ ፍላጎትን ያገናዘበ የሃርድዌር፣ የኔት ወርክና የሲስተም ድጋፍ አገልግሎት የመስጠት ሥራ ተከናውኗል፡፡

58. በባንኩ ውስጥ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን፣ የሪስክ (የሥጋት) ማነጅመንትና የውስጥ ቁጥጥር ሥራዎች የበለጠ እንዲጠናከሩና መልካም ተሞክሮዎችንና ዓለም አቀፍ መርሆችን የተከተሉ አሠራሮች በሁሉም የባንኩ የሥራ ክፍሎች እንዲተገበሩ ሥጋትን መሠረት ያደረገ የውስጥ ኦዲትና ሪስክ ማነጅመንት ትንተና ሪፖርቶች ተዘጋጅተዋል፡፡ በኦዲት ግኝቶች ላይ ተመስርተው የቀረቡ ምክረ ሐሳቦች ትግበራን በተመለከተም በየጊዜው ክትትል ተደርጓል፡፡

59. የባንኩ መመሪያዎች፣ ውሣኔዎች፣ ትዕዛዞችና ውሎች ተፈፃሚነት በሥራ ላይ ካሉት ሕጎች ጋር ተስማሚ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በወጣው ዕቅድ መሠረት የሕግ ክትትል ተደርጓል፡፡ ከዚህ ሌላ የሕግ አስተያየቶችና ምክሮች በፅሑፍ ለውስጥና ለውጭ ደንበኞች ተሰጥተዋል፡፡

## 2.5 *<u>የባንኩን የፋይናንስ አስተዳደር ማሻሻል</u>*

60. በ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ስድስት ወራት ይገኛል ተብሎ የታቀደው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የገቢ መጠን ብር 6.32 ቢሊዮን ሲሆን፣ የተሰበሰበው ግን ብር 4.14 ቢሊዮን ያህል ነው፡፡ ይህ አፈፃፀም ከዕቅዱ አኳያ ሲታይ በብር 2.18 ቢሊዮን ወይም 34.6 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ ይህ

ሲሆን የቻለው በውጪ ምንዛሪ መዋዠቅ ምክንያት የደረሰው ኪሣራ ከዕቅዱ በብር 3.5 ቢሊዮን ከፍ በማለቱ ነው፡፡ በአንፃሩ ከወለድ፣ ከውጭ ምንዛሪ ኮሚሽን፣ ከአገልግሎት ክፍያና ከልዩ ልዩ ገቢዎች የተገኘው ገቢ ዕድገት አሳይቷል፡፡

61. በሌላ በኩል፣ ለበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት የታቀደው መደበኛ ወጪ ብር 7.64 ቢሊዮን ሲሆን፣ የተደረገው ወጪ ብር 6.75 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ በመሆኑም የመደበኛ ወጪ ክንውን ከዕቅዱ በብር 886.7 ሚሊዮን ወይም 11.6 በመቶ ያንሳል፡፡ ለዚህም ዋና ምክንያት ለወለድ የተከፈለው ብር 4.3 ቢሊዮን ከዕቅዱ የብር 1.4 ቢሊዮን ቅናሽ በማሳየቱ፣ እንዲሁም ለሣንቲም ቀረጻ የተያዘው በጀት ብር 312.3 ሚሊዮን ቢሆንም የወጣው ወጪ ግን ብር 111.9 ሚሊዮን ብቻ በመሆኑ ነው፡፡

62. የካፒታል ወጪን በተመለከተ ለመጀመሪያው ስድስት ወራት የተያዘው በጀት ብር 180.1 ሚሊዮን ሲሆን፣ አጠቃቀሙ ብር 47.5 ሚሊዮን ወይም 26.3 በመቶ ብቻ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ለባንኩ ነባር ሕንፃ ዕድሳትና ተዛማጅ ሥራዎች፣ ለጄነሬተር ግዢዎች፣ ለዋናው የመረጃ (ዳታ) ማዕከል ፕሮጀክት እና ለአቃቂ ካምፓስ ዕድሳትና ዲዛይን ዕድሳት የተያዘው በጀት ገና ሥራ ላይ ባለመዋሉ ነው፡፡

63. በመሆኑም ባንኩ በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የብር 2.6 ቢሊዮን የተጣራ ኪሳራ አሳይቷል፡፡ ይህም ኪሣራ ከዕቅዱ በ98.4 በመቶ ይበልጣል፡፡

**የፋይናንስ □ቅ□ አፈፃፀም**
**(ከሐምሌ 2013 — ታህሣሥ 2014)**

**(በሺህ ብር)**

| የገቢና ወጪ መደብ | የ2014 በጀት ዓመት የስድስት ወራት ዕቅድ | የስድስት ወራት ዕቅድ ክንውን | ክንውን በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| | (ሀ) | (ሐ) | ሐ-ሀ / ሀ |
| ጠቅላላ ገቢ | 6,321,971.3 | 4,135,564.2 | 65.4 |
| መደበኛ ወጪ | 7,642,993.1 | 6,756,259.3 | 88.4 |
| የካፒታል ወጪ | 180,151.3 | 47,457.2 | 26.3 |
| የተጣራ ገቢ | (1,321,021.76) | (2,620,695.05) | (98.4) |

## III. ማጠቃለያ፡- የተከናወኑ ዐበይት ተግባራት፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

### 3.1 የተከናወኑ ዐበይት ተግባራት

64. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ካቀዳቸው ተግባራት አብዛኞቹን አከናውኗል፡፡ ከእነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ባንኩ የዋጋ ንረትን ለማርገብ የተለያዩ የገንዘብ ፖሊሲ መሣሪያዎችንና አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የወሰደ ቢሆንም፣ የዋጋ ግሽበት ዋና ተግዳሮት ሆኖ ቀጥሏል፡፡ ለዚህ የዋጋ ግሽበት መንሥኤው በዋናነት ምግብ ነክ የዋጋ ግሽበት ነው፡፡

- ባንኩ የወለድ ተመንና የብር የውጭ ምንዛሪ ተመን እንቅስቃሴ በዕቅዱ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ክትትል አድርጓል፡፡

- የፋይናንስ ተቋማትን የአገልግሎት አሰጣጥ፣ ተደራሽነትና አካታችነት፣ እንዲሁም ቅልጥፍናና ውጤታማነት ለማሻሻል የክትትልና የቁጥጥር እርምጃዎች የተወሰዱ ሲሆን፣ የፋይናንስ ዘርፉ ጤናማ፣ የተረጋጋና ትርፋማ ሆኖ ቀጥሏል፡፡

- ቅድሚያ ለሚሰጣቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች በቂ የብድር አቅርቦትና የውጭ ምንዛሪ እንዲኖር በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት አቅም በፈቀደ መጠን የሀገር ውስጥ ብድርና የውጭ ምንዛሪ የማቅረብ ሥራ ተከናውኗል፡፡

- ዘመናዊ፣ ደህንነቱ የተጠበቀና አስተማማኝነቱ የተረጋጋጠ የክፍያ ሥርዓት ለማስፈን ባንኩ የተለያዩ የክትትልና ግምገማ ሥራዎችን አከናውኗል፡፡

- በኢኮኖሚው ውስጥ በቂ የገንዘብ አቅርቦት መኖሩን ከማረጋገጥ ባሻገር፣ የአዲስ ብር ኖቶች ስርጭት እንዲሁም አሮጌ የብር ኖቶችን የመሰብሰብና በከፊል የማስወገድ ሥራዎች በዕቅዱ መሠረት ተከናውነዋል፡፡

- የባንኩን የአገልግሎት አሰጣጥና የአሠራር ቅልጥፍና ለማሻሻል የውጤት ተኮር የሥራ ምዘና ሥርዓት በሁሉም የባንኩ የሥራ ክፍሎች እየተተገበረ ይገኛል፡፡

## 3.2 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

65. በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት ባንኩን ካጋጠሙት ተግዳሮቶች መካከል ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ/ የዋጋ ንረት ከነጠላ አሃዝ በላይ መሆን፣

ለ/ የውጭ ምንዛሪ ፍላጎትና አቅርቦት አለመመጣጠን፣

ሐ/ የወጪ ንግድ ዕድገት ቢኖርም፣ የሁሉም ወጪ ምርቶች አፈፃፀም የተጠበቀውን ያህል አመርቂ አለመሆን፣

መ/ በኮቪድ-19 መከሰት ምክንያት በሙሉ አቅም መሥራት አለመቻል፣

ሠ/ የሠለጠነና በቂ ልምድ ያለው የሰው ኃይል እጥረት፡፡

ባንኩ እነዚህን ዐበይት ችግሮች ለመቅረፍ አቅም የፈቀደውን ያህል በመንቀሳቀስ አንዳንድ ለውጦችን ለማስመዝገብና ችግሮቹ እንዳይባባሱ ለማድረግ ችሎአል፡፡ ለምሣሌ ያህል፡-

- የዋጋ ንረትን ለማርገብ ጥብቅ የገንዘብና የፊስካል ፖሊሲዎች በቅንጅት ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ ይህም እርምጃ በቀሩት ወራት ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

- ከወጪ ንግድ የተገኘው የውጭ ምንዛሪ በግማሽ ዓመቱ መጨረሻ የ21.3 በመቶ ዕድገት ቢያሳይም፣ ከሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ የማመንጨት እምቅ አቅምና ከዕድገት ፍላጎት አንፃር በቂ አይደለም፡፡ ስለሆነም የወጪ ንግድ አፈፃፀምን ለማሻሻል፣ የሐዋላ ግኝትና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ለማጠናከር ሁሉም ባለድርሻ አካላት በቅንጅት ሊሠሩ ይገባል፡፡ ብሔራዊ ባንክ በበኩሉ የወጪ ንግድ ተወዳዳሪነትን ለማበረታታት የብር የውጭ ምንዛሪ ተመን ከአሜሪካን ዶላር አኳያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲቀንስ ያደረገ ሲሆን፣ ለወደፊቱም በጥናት ላይ የተመሠረቱ የፖሊሲና አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

- ባንኩ ነዳጅና ሌሎች ምግብ ነክ የሆኑ መሠረታዊ ሸቀጦችን ከውጭ ለማስገባት፣ እንዲሁም ለውጭ ዕዳ ክፍያ ቅድሚያ መስጠቱ ተገቢ ቢሆንም፣ ከውጭ ምንዛሪ እጥረት አኳያ በአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ክምችትና በከረንት አካውንት ሚዛን ላይ ተጨማሪ ጫና አሳድሯል፡፡

- የሰው ኃይል ችግርን ለመቅረፍ ባንኩ በስድስት ወራት ውስጥ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት አዳዲስ ሠራተኞችን በተፈለገው መጠን ለመቅጠር ባይችልም፣ ክፍት የሥራ መደቦችን ከውስጥ የመሙላትና ቁልፍ በሆኑ የሥራ መደቦች ላይ የአገልግሎት አሰጣጡ ሳይስተጓጎል

እንዲቀጥል የማድረግ ሥራ አከናውኗል፡፡ በቀሩት ወራት ግን አዳዲስ ሠራተኞችን ለመቅጠር ዝግጅት እያደረገ ይገኛል፡፡ ከዚህ ሌላ፣ የሠራተኞችን ዕውቀትና ክህሎት ለማሻሻል ሠራተኞች በአገር ውስጥና በውጭ አገር ልዩ ልዩ ሥልጠናዎችንና የልምድ ልውውጥ ዕድሎችን እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም፣ በተከሰተው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት አፈፃፀሙ ዝቅተኛ ሆኗል፡፡

66. በጥቅሉ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በ**2014** በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ለመሥራት በዕቅድ ከያዛቸው የኢኮኖሚ ማሻሻያና መደበኛ ተግባራት መካከል አብዛኞቹን በዕቅዱ መሠረት ያከናወነ ሲሆን፣ በተለያዩ ምክንያቶች በተለይም በኮቪድ-19 ምክንያት ያልተከናወኑትን ተግባራት በቀጣዮቹ ወራት ለመተግበር ጥረቱን የሚቀጥል ይሆናል፡፡

# የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
# የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ዕቅድ አፈፃፀም

| እይታ | ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም መግለጫ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የስድስት ወራት ዕቅድ | የስድስት ወራት ክንውን | ልዩነት | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. ተገልጋዮች | 1.1 | የዋጋ መረጋጋትን ማስፈን | የሪዘርቭ ገንዘብ ዕድገትን ከዋጋ ንረት ግብ ጋር የተጣጣመ ማድረግ | | - ከዋጋ ንረት ጋር የተጣጣመ የሪዘርቭ ገንዘብ ዕድገት | ከግቡ ያለው ልዩነት | 9.5% | 25.8% | 16.3% | 9.5% የዓመት ዕቅድ ሲሆን፣ አሁን በሀገራችን በሰሜኑ ክፍል አለመረጋጋት ምክንያት በዓመቱ መጨረሻ ዕድገቱ ከዚህ ከፍ ያለ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ |
| | | | | | - የሪዘርቭ ገንዘብ እንቅስቃሴ ትንተና ሪፖርት | የሪፖርት ጥራትና ብዛት | 6 | 6 | የለም | |
| | | | | | - የዋጋ ንረት ትንተናና ትንበያ ሪፖርት | የሪፖርት ጥራትና ብዛት | 6 | 6 | የለም | |
| | 1.2 | ከፍተኛና ቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስገኘት | ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ዘርፎች በቂ የብድር አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ | - ብር 46.9 ቢሊዮን ብድር ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ዘርፎች እንዲቀርብ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል | - የብድር አቅርቦት | የተቀመጠ ብድር ግብ | ብር 33 ቢሊዮን | ብር 46.9 ቢሊዮን | ብር 13.9 ቢሊዮን | |
| | | | | - መንግሥት ከብሔራዊ ባንክ የተበደረው ገንዘብ መጠን በዕቅዱ መሠረት ሆኗል | ዕለታዊና ወርሀዊ ሪፖርቶች | የተወሰደ የብድር መጠን የተጣራ በብር | ብር 10.0 ቢሊዮን | ብር 21.5 ቢሊዮን | ብር 10.5 ቢሊዮን | ብር 10 ቢሊዮኑ የዓመት ዕቅድ ነው |
| | | | ለኢኮኖሚ የውጭ ምንዛሪ ማቅረብ | - ለኢኮኖሚ 2.8 ቢሊዮን ዶላር ቀርቧል፡፡ | በቂ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት | የቀረበ የውጭ ምንዛሪ | 2 ቢሊዮን ዶላር | 2.8 ቢሊዮን ዶላር | 0.8 ቢሊዮን ዶላር | ከዕቅድ በላይ |

| እይታ | ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም መግለጫ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የስድስት ወራት ዕቅድ | የስድስት ወራት ክንውን | ልዩነት | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1.3 | የውጭ ምንዛሪ ተመን ማረጋጋት | የውጭ ምንዛሪ ተመን ከተቀመጠው ግብ ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ | | እውነተኛው የውጭ ምንዛሪ ተመን ከግቡ ያለው ልዩነት መጥበብ | አፈፃፀም በመቶኛ | ±5% | -12.5% | (7.5%) | የ1ኛ ሩብ ዓመት ክንውን |
| | | | ትንበያን የያዘ የውጭ ምንዛሪ ሪፖርት ማዘጋጀት | - ሣምንታዊ የውጭ ምንዛሪ ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርት | - ሪፖርት | - የሪፖርት ጥራትና ብዛት | 26 | 26 | የለም | |
| | 1.4 | የተረጋጋ የፋይናንስ ሥርዓት ማስፈን | የተረጋጋ ፋይናንስ ዘርፍ | | - ስቴቢሊቲ ሪፖርት | - የደንበኞች እርካታ መጨመር በመቶኛ (ለባንክ) | ለባንክ 86% | 72.17% | (13.83%) | የ2013 ታህሣሥ ወር የየዳሰሳ ጥናት ውጤት |
| | | | | | | | ለኢንሹራንስ 85% | 80.24% | (6.24%) | ›› |
| | | | | | | | 80% | 79.68% | (0.32%) | ›› |
| | | | | | | - የካፒታል ብቃት | ለባንኮች ቢያንስ 8% | 16.52% | 8.52% | ከተጠበቀው በላይ ሆኗል |
| | | | | | | | ለኢንሹራንስ ቢያንስ 20% | 51% | 31% | ›› |
| | | | | | | | ለማይክሮፋይናንስ ቢያንስ 12% | 35.6% | 23.6% | ›› |
| | | | | | | | ለሊዝ ፋይናንስ ኩባንያ ቢያንስ 10% | 59.4% | 49.4% | ›› |
| | | | | | | - ዕዳን የመክፈል ህዳግ (solvency) | ለኢንሹራንስ ቢያንስ 100% | 304% | 204% | ›› |
| | | | | | | - የጥሬ ገንዘብ ነክ (liquidity) | ለባንኮች ቢያንስ 15% | 28.67% | 13.67% | ›› |
| | | | | | | | ለኢንሹራንስ ቢያንስ 100% | 104% | 4% | ከተጠበቀው በላይ ሆኗል |

| እይታ | ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም መግለጫ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የስድስት ወራት ዕቅድ | የስድስት ወራት ክንውን | ልዩነት | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ቢያንስ 20% | 42.7% | 22.7% | ›› |
| | | | | | | - የማይመለስና አጠራጣሪ ብድር ከጠቅላላ ብድር አንፃር | ለባንኮች ቢበዛ 5% | 6.02% | (1.02%) | |
| | | | | | | | ለማይክሮ ፋይናንስ ቢበዛ 5% | 8.2% | (3.2%) | |
| | | | | | | | ለሊዝ ኩባንያዎች ቢበዛ 5% | 5.8% | (0.8%) | |
| | | | የፋይናንስ አካታችነትን ማስፋፋት | ስለ ፋይናንስ አካታችነት ክትትልና ግምገማ ተደርጓል | የፋይናንስ አካታችነት አጠቃላይ ሂደት ክትትልና ግምገማ ማድረግ | የክትትልና ግምገማ ሪፖርት | 100% | 100% | የለም | |
| 2. ፋይናንስ | 2.1 | የባንኩን የፋይናንስ አስተዳደር ማሻሻል | የበጀት አጠቃቀም ሥርዓት | የባንኩ ወርሃዊና ሩብ ዓመታዊ የበጀት አጠቃቀም ሪፖርቶች ተዘጋጅተዋል | - የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት | - አፈፃፀም በመቶኛ | 50% | 50% | የለም | |
| | | | | የባንኩን ሂሳብ አያያዝ አስተማማኝነት ለማሳደግ የሚረዳ የክትትል ሪፖርት ተዘጋጅቷል | - የተዘጋጀ ሪፖርት | - አፈፃፀም በመቶኛ | 50% | 50% | የለም | |

| እይታ | ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም መግለጫ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የስድስት ወራት ዕቅድ | የስድስት ወራት ክንውን | ልዩነት | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3. የውስጥ አሠራር | 3.1 | 0 | የሀገር ውስጥ ቁጠባን ማሳደግ | ወርሃዊ የመንግሥት ቦንድ ቁጠባ ሪፖርት ተዘጋጅቶአል | - ወርሃዊ የመንግሥት ቦንድ ቁጠባ ሪፖርት | በወቅቱ በጥራት የቀረበ ሪፖርት | 6 | 6 | የለም | |
| | | | የውጭ ምንዛሪ ክምችቱን ማጎልበትና መቆጣጠር | የውጭ ምንዛሪ ክምችት ሽፋን በወር የገቢ ንግድ | - የተያዘ የውጭ ምንዛሪ መጠባበቂያ ክምችት በወር የገቢ ንግድ | የውጭ ምንዛሪ ክምችት ሽፋን በወር የገቢ ንግድ | *2.2 ወር* | *1.3 ወር* | *(0.9 ወር)* | |
| | | | -በቂ የውጭ ምንዛሪ ክምችት መኖሩን ማረጋገጥ | የውጭ ምንዛሪ ክምችት ማስተዳደር | - ደህንነቱ የተጠበቀ የውጭ ምንዛሪ ክምችት | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | ወርሃዊ የውጭ ንግድ ሁኔታ ትንተና | - የውጭ ንግድ ሁኔታ ትንተና | የቀረበ ሪፖርት ጥራትና ብዛት | 6 | 6 | የለም | |
| | | | - በቂ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማረጋገጥ | ወርሃዊ የወጪ ንግድና የግል ሃዋላ ስታትስቲክስ ተሰብስቧል፡፡ | - ወርሃዊ የወጭ ንግድ ሁኔታ ትንተና ሪፖርት | የቀረቡ የትንተና ሪፖርቶች ብዛት | 6 | 6 | የለም | |
| | 3.2 | የገንዘብ አስተዳደር (monetary management) ቅልጥፍናና ውጤታማነት ማሻሻል | አስተማማኝ የገንዘብ ትንተና ሪፖርት መኖሩን ማረጋገጥ | አስተማማኝ የገንዘብ ትንተና ሪፖርት መኖሩን ማረጋገጥ | የገንዘብ አመልካቾችና የሪዘርቭ ገንዘብ ዒላማ የተቀማጭ ሂሳብ መጠን የሚገልጽ ሪፖርት | የቀረቡ የትንተና ሪፖርቶች ብዛት | 6 | 6 | የለም | |
| | 3.3 | የፋይናንስ ተቋማት ቁጥጥር ውጤታማነት ማጠናከር | የባንክ ቁጥጥር ውጤታማነት ማጠናከር | የይገባኛል ጥያቄ ስላልቀረበባቸው ተከፋይ ሂሳቦች፤ የባንኮች የውስጥ ኦዲት፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ወደ ባንክ የሚሸጋገሩበት እና ባንኮች ከሦስተኛ አካል በውጭ ምንዛሪ ብድር እንዲበደሩ የሚያስችል መመሪያዎች ማውጣት እና የውጭ ምንዛሪ ይዞታ መመሪያ ክለሳ ማድረግ፣ | የይገባኛል ጥያቄ ስላልቀረበባቸው ተከፋይ ሂሳቦች፤የባንኮች የውስጥ ኦዲት፣ አነስተኛ የፋይናንስ ወደ ባንክ የሚሸጋገሩበት እና ባንኮች ከሦስተኛ አካል በውጭ ምንዛሪ ብድር እንዲበደሩ የሚያስችል መመሪያዎች ማውጣት እና የውጭ ምንዛሪ ይዞታ መመሪያ ክለሳ ማድረግ | የወጣ መመሪያ | 2 | 7 | 5 | ከዕቅድ በላይ ተሥርቷል |

| እይታ | ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም መግለጫ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የስድስት ወራት ዕቅድ | የስድስት ወራት ክንውን | ልዩነት | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የባንክ ዘርፍ ጤንነት ሪፖርት እና እያንዳንዱን ባንክ በተናጠል የመመዘን ሥራ ተሠርቷል | በሁለተኛ ሩብ ዓመት የሚዘጋጅ የባንክ ዘርፍ ጤንነት ሪፖርት | የተዘጋጀ የባንክ ዘርፍ ጤንነት ሪፖርት ብዛት | 2 | 2 | የለም | |
| | | | | ወርሃዊ የተቀማጭ፣ የብድር፣ የካፒታልና የሀብት ዕድገት ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡ | በሁለተኛ ሩብ ዓመት የሚዘጋጅ የተቀማጭ እና ብድር ስርጭት ሪፖርት፤ | የተዘጋጀ የተቀማጭ እና ብድር ስርጭት ሪፖርት ብዛት | 6 | 6 | የለም | |
| | | | | በቦታው በመገኘትና የአደጋ ተጋላጭነትን መሠረት በማድረግ ባንክ ላይ የቁጥጥር ሥራ ተሠርቷል፡፡ | የተዘጋጀ የምርመራ ዉጤት ሪፖርት | የተዘጋጀ ሪፖርት ብዛት | 4 | 2 | (2) | አስቸኳይ ያልታቀዱ ሥራዎች ላይ በመጠመድ እና በሥራ ብዛት |
| | | | | በቦታው በመገኘት የመስክ ክትትል ማካሄድ | የመስክ ክትትል ሪፖርት | የመስክ ክትትል ሪፖርት | 3 | 2 | (1) | በሥራ መደራረብ |
| | | | | የ2014 የባንኮች የቁጥጥር ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ | የተዘጋጀ የ2014 የባንኮች የቁጥጥር ዕቅድ | የተዘጋጀ ዕቅድ | 1 | 1 | የለም | |
| | | | | የባንኮች ተቋማዊ መረጃ ተከልሶአል | የተከለሰ ተቋማዊ መረጃ | የተከለሰ ተቋማዊ መረጃ ብዛት | 100% | 100% | የለም | |
| | | የአሠራር/የአገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍና ማሻሻል | የዳይሬክቶሬቱን አገልግሎት ማሻሻል | የባንኮች የሥራ ፈቃድ ታድሷል፣ የቅርንጫፍ እና ንዑስ ቅርንጫፍ ባንኮች የሥራ ፍቃድ እንዲሁም አዲስ ቅርንጫፎች ንዑስ ቅርንጫፎች እንዲከፈቱ ፈቃድ ተሰጥቷል | የታደሰ የባንክ ሥራ እና የተሰጠ የቅርንጫፍ ፈቃድ | በዜጎች ቻርተር መሠረት | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | ምስረታ ላይ ላሉ ባንኮች አስፈላጊውን እገዛ በማድረግ የሥራ ፈቃድ መስጠት | አዲስ ለሚቋቋሙ 2 ባንኮች እና 2 ከአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋም ወደ ባንክ ላደጉ የተሰጠ የሥራ ፈቃድ | በዜጎች ቻርተር መሠረት | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | የባንኮችን ዋና እና ከፍተኛ የሥራ አስፈፃሚዎች እና የዳይሬክተር ሹመት የማፅደቅ ሥራ ተሠርቷል፡፡ እንዲሁም ባንኮችን የዉጭ ኦዲተር ሹመት አፅድቋል፡፡ | የፀደቀ የውጭ ኦዲተር፣ የባንክ ዋና እና ምክትል ሥራ አስፈፃሚና፣ የዳይሬክተሮች ሹመት፣ | በዜጎች ቻርተር መሠረት | 100% | 100% | የለም | |

| እይታ | ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም መግለጫ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የስድስት ወራት ዕቅድ | የስድስት ወራት ክንውን | ልዩነት | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዘመናዊ የብድር መረጃን ለማጠናከር ለባንኮች ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡ | የተጠናከረ የብድር መረጃ እና ለባንኮች የተሰጠ ድጋፍ | በዜጎች ቻርተር መሠረት | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ከቴክኒካል ባለሙያዎች ደረጃ የምክክር መድረክ ተካሂዷል | የተካሄዱ የጋራ የምክክር መድረኮች | የተዘጋጁ የምክክር መድረኮች ብዛት | 1 | 0 | (1) | በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት |
| | 3.4 | የፋይናንስ ተቋማትን ሱፐርቪዥን ውጤታማነት ማጠናከር | የኢንሹራንስ ሱፐርቪዥን ማጠናከር | በ3 ኢንሹራንስ ኩባንያዎች ላይ የመስክ ሥራ ተጠናቋል | የመስክ ምርመራ ሪፖርት | የሪፖርት ብዛት | 3 | 3 | የለም | ከ2013 በጀት ዓመት የዞረ |
| | | | | በሌሎች 2 ኢንሹራንስ ኩባንያዎች ላይ የመስክ ምርመራ ሪፖርቶች የተጠናቀቁ ሲሆን፣ የሌላ 1 ኢንሹራንስ ኩባንያ ሪፖርት 75 በመቶ ተጠናቋል | የመስክ ምርመራ ሪፖርት | የሪፖርት ብዛት | 3 | 2 =100%<br>1 = 75% | የለም<br>25% | |
| | | | | በ3 ኢንሹራንስ ኩባንያዎች ላይ የክትትል ሪፖርቶች የተዘጋጁ ሲሆን፣ በሌላ 1 ኢንሹራንስ ኩባንያ ላይ የክትትል ሪፖርቱ አልተዘጋጀም | የክትትል ሪፖርቶች | የሪፖርት ብዛት | 4 | 3 =100%<br>1 = 0% | የለም<br>100% | |
| | | | | በኢንሹራንስ ዘርፍ ላይ 2 የመስክ ውጭ ምርመራ ሪፖርቶች ተጠናቀዋል | የመስክ ውጭ የምርመራ ሪፖርት | የክትትል ሪፖርት | 2 | 2 | የለም | |
| | | | | የእያንዳንዱ ኢንሹራንስ ኩባንያ የተቋም መግለጫ (Institutional Profile) ወቅታዊ የማድረግ ሥራ ተጠናቋል | ወቅታዊ የሆነ የተቋም ይዘት (Institutional Profile) መግለጫ ሪፖርት | የተዘጋጀ ሪፖርት | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | የኢንሹራንስ ሱፐርቪዥን ዕቅድ ተዘጋጅቷል | የሱፐርቪዥን ዕቅድ | የተዘጋጀ የሱፐርቪዥን ዕቅድ | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | የውጭ ኦዲተር ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጅቷል | ረቂቅ መመሪያ | ረቂቅ መመሪያ | 1 | 1 | የለም | |

| እይታ | ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም መግለጫ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የስድስት ወራት ዕቅድ | የስድስት ወራት ክንውን | ልዩነት | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የመድን ሰጪዎችን የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ስጋት ተኮር እንዲሆን የሚያስገድድ ረቂቅ መመሪያ 90 በመቶ ተጠናቋል | ረቂቅ መመሪያ | ረቂቅ መመሪያ | 1 | 1=90% | 10% | |
| | | | | የመድን አገልግሎቶችን ፈቃድ ለመስጠት የሚያግዝ ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጅቷል | ረቂቅ መመሪያ | የወጣ መመሪያ | 1 | 1 | የለም | |
| | | | | ኢንሹራንስ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ልማት ባንክ ቦንድ ላይ ኢንቨስት ስለሚያደርጉበት ሁኔታ የሚደነግግ መመሪያ ወጥቷል | የወጣ መመሪያ | የወጣ መመሪያ | 1 | 1 | የለም | |
| | | የባንኩን አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል | የኢንሹራንስ ሱፐርቪዥን አገልግሎት ጥራት ማሳደግ | ✓ ለአንድ ኢንሹራንስ ኩባንያ ከጠቅላላ መድን በተጨማሪ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የመድን አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ ተሰጥቷል<br>✓ ለቅርንጫፍ፣ ለመድን ደላላ እና ለመድን ወኪሎች፣ አዲስ ፈቃድ ተሰጥቷል | አዲስ የተሰጡ ፈቃዶች፣ የፈቃድ ዕድሳቶች | በዜጎች ቻርተር በተቀመጠው ጊዜ | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | ✓ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ የመድን ወኪሎች፣ የመድን ደላሎች፣ /ጉዳት ገማቾች እና የመድን መርማሪዎች ፈቃድ ታድሷል | የፀደቁ ቃለ ጉባኤዎች፣ ዋና እና ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ ሹመቶች | በዜጎች ቻርተር በተቀመጠው ጊዜ | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | ✓ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ የባለአክስዮኖች መደበኛ እና አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ቃለ-ጉባኤዎች፣ የአስተዳደር ቦርድ ቃለ ጉባኤዎች፣ የኩባንያ ቦርድ አባላት፣ ዋና እና ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ ሹመቶች ፀድቀዋል | የፀደቁ ቃለ ጉባኤዎች፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ዋና እና ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ ሹመቶች | በዜጎች ቻርተር በተቀመጠው ጊዜ | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | ✓ ለኢንሹራንስ ኩባንያዎች አዳዲስ ዓይነት የመድን ሽፋን አገልግሎቶች እንዲሰጡ ፈቃድ ተሰጥቷል | የተሰጠ የመድን ሽፋን አገልግሎት ፈቃድ | የተሰጠ የመድን ሽፋን አገልግሎት ፈቃድ | 100% | 100% | የለም | |

| እይታ | ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም መግለጫ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የስድስት ወራት ዕቅድ | የስድስት ወራት ክንውን | ልዩነት | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 3.5 | የፋይናንስ ተቋማትን ቁጥጥር ውጤታማነት ማጠናከር | አነስተኛ የፋይናንስ እና የካፒታል ዕቃዎች ፋይናንስ ተቋማት ቁጥጥር ሥራን ማጠናከር | መመሪያ ማዘጋጀት ወይም ማሻሻል | አንድ መመሪያ ማውጣት | የወጣ/የተከለሰ መመሪያ ብዛት | 2 | 2 | የለም | |
| | | | | የአነስተኛ ፋይናንስ ዘርፍ የሩብ ዓመት ጤንነት ሪፖርት ማዘጋጀት | ሁለት የአ/ፋ ዘርፍ ጤንነት ሪፖርት ማዘጋጀት | የተዘጋጀ የአ/ፋ ዘርፍ ጤንነት ሪፖርት ብዛት | 2 | 2 | የለም | |
| | | | | የሊዝ ፋይናንስ ዘርፍ የሩብ ዓመት ጤንነት ማዘጋጀት | ሁለት የሊዝ ፋይናንስ ዘርፍ ጤንነት ሪፖርት ማዘጋጀት | የተዘጋጀ የሊዝ ፋይናንስ ዘርፍ ጤንነት ሪፖርት ብዛት | 2 | 2 | የለም | |
| | | | | የዳይሬክቶሬቱን የoff-site ሥራዎችን በዘመነ ሲስተም ጥብቅ ክትትል ማድረግ፡ | የዳይሬክቶሬቱ off-site ሥራ ዘመናዊ ሲስተም የተደገፈ ማድረግ | የoff-site ሥራ ማዘመን □ሮጀክት መጠናቀቅ | 100% | 98% | (2%) | |
| | | | | በአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ላይ የመስክ ቁጥጥር ሥራ መስራት | የመስክ ቁጥጥር ሪፖርት ማዘጋጀት | የመስክ ቁጥጥር ሪፖርት ብዛት | 7 | 8 | +1 | |
| | | | | በአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ላይ የመስክ ክትትል ምርመራ መሥራት | የክትትል ምርመራ ሪፖርት ማዘጋጀት | የክትትል ምርመራ ሪፖርት ብዛት | 4 | 3 | (1) | |
| | | | | የሊዝ ኩባንያዎች ላይ የመስክ ቁጥጥር ሥራ መስራት | የመስክ ቁጥጥር ሪፖርትማዘጋጀት | የመስክ ቁጥጥር ሪፖርት ብዛት | 1 | 1 | የለም | |
| | | | | በተቋማት ላይ የሚወሰዱ የቁጥጥር እና የእርምት እርምጃዎችን ማጠናከር | በወቅቱ የተወሰደ እርምጃ | በወቅቱ የተወሰደ እርምጃ | አንድ ሳምንት | አንድ ሳምንት | የለም | |
| | | | | የተቋማቱን የውጭ ኦዲተር ሹመት የማፅደቅ | የፀደቁ ሰነዶችና ሹመቶች | በአንድ የሥራ ቀን | 1 የሥራ ቀን | 1 የሥራ ቀን | የለም | |
| | | | | ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመት፣ የስድስት ወራት እና የዓመት አፈፃፀም ሪፖርቶችን ማዘጋጀት | ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመት፣ የስድስት ወራት እና የዓመት አፈፃፀም ሪፖርቶችን በወቅቱ ማቅረብ | በወቅቱ የተዘጋጁ ሪፖርቶች | 100% | 100% | የለም | |

| እይታ | ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም መግለጫ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የስድስት ወራት ዕቅድ | የስድስት ወራት ክንውን | ልዩነት | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ወቅታዊና የተጠናከረ ተቋማዊ መረጃ (Institutional Profile) ማዘጋጀት | ወቅታዊና የተጠናከረ ተቋማዊ መረጃ (Institutional Profile) | ጥራቱንና ጊዜውን ጠብቆ የተዘጋጀ ተቋማዊ መረጃ | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | የተናጠል አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት **የ"CAMEL"** ሪፖርት ማዘጋጀት | የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም "CAMEL" ሪፖርት ማዘጋጀት | በወቅቱ የተዘጋጁ ሪፖርቶች | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | - አዲስ ለሚቋቋሙ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት/ሊዝ ኩባንያዎች የሥራ ፈቃድ መስጠት | - አዲስ ለሚቋቋሙ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት/ሊዝ ኩባንያዎች የተሰጠ የሥራ ፈቃድ | በዜጎች ቻርተር መሠረት | 60 የሥራ ቀናት | 60 የሥራ ቀናት | የለም | |
| | | | | - የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት/ሊዝ ኩባንያ ኃላፊዎችን ሹመት ማፅደቅ | - የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት/ሊዝ ኩባንያ ኃላፊዎች ሹመት | የተሰጠ/የፀደቀ ሹመት በዜጎች ቻርተር መሠረት | በ15 የሥራ ቀናት | በ15 የሥራ ቀናት | የለም | |
| | 3.6 | የክፍያ ሥርዓቱን ደህንነት፣ አስተማማኝነትና ቅልጥፍና ማሻሻል | የክፍያ ሥርዓቱን ደህንነት፣ አስተማማኝነትና ቅልጥፍና ማሻሻል | - የክፍያ ሥርዓቱን የመከታተልና፣ የማስተዳዳር ተግባር ተከናውኗል | - በአግባቡ የሚመራና በመደበኛነት ክትትል የተደረገበት የክፍ ያ ሥርዓት | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | - የክፍያ ሥርዓት ክትትል ዕቅድ ማውጣት | - የክትትልና ሪፖርት ማውጣት | የተዘጋጀ የክፍያ ሥርዓት ዕቅድ | 1 | 1 | የለም | |
| | | የአገልግሎት አሠጣጥ ቅልጥፍናን ማሻሻል | የሥራ ሂደቱን አገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍና ማሻሻል | - በዕቅዱ መሠረት የግምጃ ቤት ሰነዶች ጨረታ ተከናውነዋል፡፡ | - የተካሄዱ ጨረታዎች | የተካሄዱ ጨረታዎች በቁጥር | 20 | 20 | የለም | |
| | | | | የተለያዩ ከባንኪንግ ጋር የተያያዙ መረጃዎች ደንበኞች በጠየቁ ጊዜ ተሰጥቷል፡፡ | - መረጃና ድጋፍ ለሚፈልጉ ደንበኞች ወቅታዊ የሆነ ምላሽ መስጠት | የተሰጠ መረጃና ድጋፍ | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | | - በመንግሥት በፋይናንስ ተቋማት ሂሳቦች ላይ መደበኛ የባንክና የክፍያ አገልግሎት መስጠት | በተለጠጠ ግብ የተሰጠ አገልግሎት | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | የማዕከላዊ ስዊች አሠራርንና የ□ሮጀክት አፈፃፀምን መከታተልና መምራት | - ወቅቱን የጠበቀ የክትትል ሪፖርት | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | የለም | |

| እይታ | ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም መግለጫ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የስድስት ወራት ዕቅድ | የስድስት ወራት ክንውን | ልዩነት | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 3.7 | የከረንሲ አስተዳደር ሥርዓትን ዘመናዊ ማድረግ | የከረንሲ አስተዳደር ሥርዓትን ዘመናዊ ማድረግ | የገንዘብ ሕትመት/ቀረጻ ሥራ ተከናውኗል፡፡ | የተከናወነ ሕትመት/ ቀረጻ | የዕቅድ አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | የገንዘብ ስርጭት ተከናውኗል | የተሠራጨ ገንዘብ | የዕቅድ አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | አሮጌ ገንዘብ የመቁጠር፣ የመምረጥ፣ እና የመቀበል ሥራ ተከናውኗል | የተመረጠ ገንዘብ | >> | 100% | 116.82% | 16.82% | |
| | | | | አሮጌ ገንዘብ የማስወገድ ሥራ መሥራት | የተወገደ አሮጌ ገንዘብ | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 64.8% | (35.2%) | በገንዘብ ማስወገጃ ማሽን ብልሽት ምክንያት |
| | | | | ሐሰተኛ የብር ኖቶችን በተመለከተ ሪፖርት ተዘጋጅቷል | የተዘጋጀ ሪፖርት | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | የወርቅ ግዥን ማከናወን | የተገዛ ወርቅ | የዕቅድ አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | የለም | |
| | 3.8 | የፋይናንስ አካታችነትን ማስፋፋትና ማሳደግ | የፋይናንስ ተደራሽነትና ተጠቃሚነትን ማስተባበር፣ መገምገም መቆጣጠር | ብሔራዊ የፋይናንስ አካታችነት አጠቃላይ ሂደት መከታተልና መገምገም | - የክትትልና ግምገማ ሪፖርት | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | የፋይናንስ አካታችነት አጠቃላይ ገጽታ የሚያመላክት (ከተደራሽነትና ከተጠቃሚነት) ሪፖርት ማዘጋጀት | - የተዘጋጀ ሪፖርት | የቀረበ ሪፖርት | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | የማማከርና መረጃ የመስጠት አገልግሎት | - የተዘጋጀ ሪፖርት | የቀረበ ሪፖርት | 100% | 100% | የለም | |

| እይታ | ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም መግለጫ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የስድስት ወራት ዕቅድ | የስድስት ወራት ክንውን | ልዩነት | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 3.9 | | የሰው ኃይል አገልግሎትና ክህሎት ማሳደግ | - 156 ክፍት የሥራ መደቦች በቅጥር' በተጠባባቂነትና በዝውውር ተሟልተዋል | - የተሞሉ ክፍት የሥራ መደቦች | የተሞሉ የሥራ መደቦች | 355 | 156 | (199) | የ100 ሴኩሪቲ ኦፊሰሮች ቅጥር ለማጠናቀቅ ጊዜ በመውሰዱ |
| | | | | | - የ2014 የሥልጠና ዕቅድ | የዕቅድ ሠነድ | 1 | 1 | የለም | |
| | | | | | - የሠራተኞች ሥልጠና ማካሄድ | የሥልጠናዎች ብዛት | - | 59 በአገር ውስጥና 23 በሽርቹዋል | የለም | |
| | | | | ወርሃዊ የባንኩ ሠራተኞች አጠቃላይ መረጃ ሪፖርት ተሠርቷል | - ወርሃዊ ሪፖርት ማዘጋጀት | የተዘጋጁ ሪፖርቶች ብዛት | 6 | 6 | የለም | |
| | 3.10 | | የግዥና ንብረት አገልግሎት ጥራትና ፍጥነት መጨመር | - የ2014 በጀት ዓመት የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀት | - የግዥ ዕቅድ | ብዛት | 1 | 1 | የለም | |
| | | | | ጥራት ያላቸው ዕቃዎችን፣ ሥራዎችንና አገልግሎቶችን ግዢ መፈፀም | -ጥራት ያላቸው ዕቃዎችን፣ ሥራዎችንና አገልግሎቶችን ግዢ ማከናወን | አፈፃፀም በመቶኛ | 50% | 45% | (5%) | |
| | | | | - የባንኩን የግንባታና ሌሎች ፕሮጀክቶች አፈፃፀም መከታተል | - የተደረገ ክትትል | በጊዜ መጠናቀቅ | 100% | 100% | የለም | |
| | | | የትራንስፖርት፣ የጥገናና የሴኩሪቲ አገልግሎት | የትራንስፖርት፣ የጥገናና ዕድሳት እንዲሁም የሴኩሪቲ አገልግሎት ተሰጥቷል | - በጊዜ የተሰጠ አገልግሎት | የተሰጠ አገልግሎት | 100% | 100% | የለም | |
| | 3.11 | | የኢንፎርሜሽን ሥርዓት አስተዳደር ቅልጥፍናና ውጤታማነት ማሻሻል | – ደህንነቱ የተጠበቀ የኢንፎርሜሽን ሲስተም | - የኢንፎርሜሽን ሲስተም ደህንነት ማጠናከር | የተጠናከረ ሴኩሪቲ ሲስተም | 99% | 99% | የለም | |
| | | | | - ሴኩሪቲው የተጠበቀ የኔትወርክ ኢንፍራስትራክቸርና ሲስተም ማሻሻልና □ሮጀክት መከታተል | – በዕቅዱ መሠረት መጨረስ | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | የለም | |

| እይታ | ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም መግለጫ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የስድስት ወራት ዕቅድ | የስድስት ወራት ክንውን | ልዩነት | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | - የኢንፎርሜሽን ስርጭትና ተደራሽነት ማስፋትና ዘመናዊ ማድረግ | – የተተገበረ ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | - የተጠቃሚን ፍላጎት ማዕከል ያደረገ የድጋፍና የጥገና አገልግሎት መስጠት | – ተደራሽ ኢንፎርሜሽን | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | - የአይቲ ፖሊስና መመሪያ መከለስ | – የተከለሰ መመሪያ | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | - አይቲ ሱፐርቪዥን በንግድ ባንኮች ላይ ማካሄድ | – ሱፐርቫይዝ የተደረጉ ንግድ ባንኮች | ›› | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | - የኢንፎርሜሽን ሲስተም ዕውቀት ማዳበር | – የሰለጠኑ ሠራተኞች ብዛት | የሠልጣኞች ብዛት | 100% | 100% | የለም | |
| | 3.12 | | በቂ የሆነ የሕግ ማዕቀፍ መኖሩንና መፈፀሙን ማረጋገጥ | - አዳዲስ ሕጎች ሲወጡ የሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች እንዲያውቁት ተደርጓል | – ከባንኩ ሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሕጎች ተከታትሎ ማወቅና ለሚመለከታቸው ማሳወቅ | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | የለም | |
| | | | የባንኩ መመሪያዎች፣ ውሣኔዎችና ውሎች መከበራቸውን ማረጋገጥ | - የሕግ አስተያየቶች እና ምክሮች ተሰጥተዋል፡፡ | የተሰበሰቡ ሕግ ነክ መረጃዎችና ሊስቶች የተሰጠ የሕግ አስተያየቶች | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | የለም | |
| | | | የባንኩ ጥቅም መከበሩን ማረጋገጥ | - የባንኩ ጥቅም መከበሩን ለማረጋገጥ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ማስረጃዎች መተንተንና ለፖሊሲ ሪፖርት ማዘጋጀት | ክትትል የተደረገባቸው የፍትሐ ብሔርና የወንጀል ጉዳዮች | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | የለም | |

| እይታ | ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም መግለጫ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የስድስት ወራት ዕቅድ | የስድስት ወራት ክንውን | ልዩነት | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 3.13 | የአሠራር የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል | ከለውጥ እና መልካም አስተዳደር አኳያ የባለድርሻ አካላትን እርካታ ማሳደግ | የዜጎች ቻርተር ሰነድን ማሻሻል፣ማሳተም እና ማሰራጨት | የተሻሻለ የታተመ የተሰራጨ ሰነድ | አፈጻጸም በመቶኛ | 100% | 75% | (25%) | ረቂቅ ሠነድ ለማነጅመንት ቀርቦ እየተገመገመ ስለሆነ |
| | | | | የባንኩ ስታንዳርድ ላይ ክትትል ማድረግ | የተደረገ ክትትል | አፈጻጸም በመቶኛ | 100% | 100% | - | |
| | | | | ኩነት አስተዳደር አገልግሎት ላይ ድጋፍ ማድረግ | የተደረገ ድጋፍ ክትትል | የደንበኛ እርካታ | 100% | 100% | - | |
| | | | | ከባንኩ ባለድርሻ አካላት ጋር የሚደረግ የውይይት የጊዜ ሠሌዳ ዕቅድ ማዘጋጀት | የተዘጋጀ ዕቅድ | በወቅቱ ተዘጋጀ ዕቅድ | 100% | 100% | የለም | |
| | | | ከዕቅድና ከአፈጻጸም ክትትል አኳያ የባለድርሻ አካላትን እርካታ ማሻሻል | የባንኩን የ2014 በጀት ዓመት የሩብ ዓመት እና ግማሽ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት | የተዘጋጀ ሪፖርት | በወቅቱ ሪፖርት ማዘጋጀት | 2 | 2 | የለም | |
| | 3.14 | | የኦዲትና የማማከር አገልግሎቶችን ቅልጥፍናና ውጤታማነት ማሻሻል | ሪስክን ማዕከል ያደረገ ኦዲት ማድረግ | የኦዲት ሪፖርት | የኦዲት ሪፖርት ብዛት | 6 | 4 | (2) | በኮቪድ-19 ምክንያት |
| | | | | የሪስክ ማነጅመንት ሪፖርት ማቅረብ | የሪስክ ማነጅመንት ሪፖርት | አፈፃፀም በመቶኛ | 2 | 2 | የለም | |
| | | | | የዓመት የተጠቃለለ ሪፖርት ማዘጋጀት | ማጠቃለያ ሪፖርት | | 1 | 1 | የለም | |
| | | | | በአሮጌ ብሮች የናሙና ቆጠራና የማስወገድ ሥራ እንዲሁም የውጭ ሀገር ገንዘብና ወርቅ ወደ ውጭ ሀገር ሲላክ በመገኘት የማረጋገጥ ሥራ መሥራት | ዕለታዊ ገለልተኛ የማረጋገጫ ሪፖርት | ዕለታዊ ገለልተኛ የማረጋገጫ ሪፖርት ብዛት | 100% | 100% | የለም | የሥራ ክፍሉ ያቀረበውን ጥያቄ በሙሉ ማስተናገድ ተችሏል፡፡ በዚህም 796 ዕለታዊ ገለልተኛ የማረጋገጫ ሪፖርት ተዘጋጅቷል |

| እይታ | ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም መግለጫ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የስድስት ወራት ዕቅድ | የስድስት ወራት ክንውን | ልዩነት | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4. መማማርና ዕድገት | 4.1 | የሠራተኞችን የቴክኒክ ብቃት አመራርና ባህል ማሻሻል | የሠራተኞችን የቴክኒክ ብቃት አመራርና ባህል ማሻሻል | የሠራተኞችንና ኃላፊዎችን ዕውቀትና ክህሎት ክፍተት መለየትና ክፍተቶቹን ለመሙላት የሚጠቅሙ የሥልጠና ዘርፎችን በመለየት ተገቢ ሥልጠና መስጠት | በጊዜ እና በጥራት ተመዝነው የተዘጋጁ ሥልጠናዎች ቁጥር | የተሰጡ ሥልጠናዎች | - | 82 (59 የአገር ውስጥና 23 ቨርቹዋል) | የለም | |
| | | | | | ሠራተኛውን ለማብቃት የተሠሩ ሥራዎች | የአፈፃፀም ክትትል | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | ለአዲስ ቅጥር ሠራተኞች በባንኩ ሥራዎች ዙሪያ መግለጫ ተሰጥቷል' የባንኩ ደንቦችና መመሪያዎች ተሰጥተዋል' የባንኩ ሠራተኞች መመሪያዎችን እንዲፈጽሙ ክትትል ተደርጓል | የሠራተኞችን ባህሪ ከባንኩ ዋና ዋና እሴቶች ጋር ማዛመድ | የመግለጫ ጥራት፣ የፈጀ ጊዜና የተሳታፊ ሠራተኞች ቁጥር | 100% | 100% | የለም | |
| | 4.2 | የመልካም አስተዳደር እና የሪስክ አስተዳደር ችሎታን ማሻሻል | የሥራ ክፍሎች ሪስክና የመቆጣጠሪያ ዘዴዎችን እንዲለዩና ሥራ ላይ እንዲያውሉ እገዛ ተደርጓል | ለባንኩ መመሪያ የሚገዛ ሠራተኛ | የተፈፀሙ ጥፋቶች ብዛት | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | የለም | በተፈፀሙ ጥፋቶች ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ተወስዷል |
| | | | የባንኩ ሠራተኞች የባንኩን መመሪያ በአግባቡ እንዲፈጽሙ ተደርጓል | ተለይተው የታወቁ ሪስኮችና የተወሰዱ እርምጃዎች | የተፈፀሙ ጥፋቶች ብዛት | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | የለም | |
| | | | | የአደጋ ተጋላጭነት መቆጣጠሪያ መርሆችን በሥራ ላይ ማዋል | ›› | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | የለም | |